በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአርሲ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአርሲ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የአርሲ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 ዓ.ም በተላለፈ መመሪያ መሰረት ‹‹በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተለመደና ዘላቂነት በሌለው የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሰራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ በኮንትራት/በጊዜያዊነት/ ቅጥር እንደማይፈጸም›› በመመሪያው የተመለከተ ቢሆንም፣ በዩኒቨርሲቲው ዋናው ካምፓስ የነፃ የህግ አገልግሎት ለሰጡ የአስተዳደር ሰራተኞች ጊዜያዊ /ኮንትራት/ ቅጥር ለመፈፀም በቅድሚያ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴርን ማስፈቀድ ሲገባ፤ ዘላቂነት ላለው የስራ መደብ ከሚኒስቴሩ ፍቃድ ውጭ 11 ለሚሆኑ የአስተዳደር ሰራተኞች በኮንትራት ቅጥር በመፈፀሙ፤ በበጀት ዓመቱ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ በሚል በናሙና በታየው መሰረት በድምሩ ብር 69,766.68 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
2. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በ13/8/03 በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ‹‹ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሠራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ›› የታዘዘ እና በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሌጂስሌሽን ደግሞ የአካዳሚክ ባለሙያዎች ግዴታዎች በሚለው ስር ተማሪዎችን

ማማከር፤ ፈተና መፈተን፤ የማስተማሪያ መሳሪያ መከለስ እና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም፣ ክፍያው በሴኔት ቋሚ ኮሚቴ ለመወሰኑ ተጠቅሶ በ4/12/08 በቁጥር 1-2/02/1498/98 ከአካዳሚክ ም/ፕረዝዳንት ለዩኒቨርሲቲው ፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በተጻፈው መሠረት ለዩኒቨርሲቲው በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የማማከር አገልግሎት /Thesis Advise/ ለሰጡ ሰባት አካደሚክ ባለሙያዎች በብር 4,320.00 ተመን፤ የፈተና አገልግሎት /Internal and External Examiners/ ለሰጡ 15 አካደሚክ ባለሙያዎች በብር 1,500.00 ተመን እና Thesis Chairperson እና proposal review አገልግሎት ለሰጡ 6 አካደሚክ ባለሙያዎች በብር 750.00 ተመን፣ በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 240,750.00 በመንግሥት የተፈቀደ ተመን ሳይኖር በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ውሳኔ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

3. ብር ብር 53,760.00 ለ4 ተጋባዥ መምህራን በመንግሥት ከተፈቀደው ተመን በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፣

4. በፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪ□ ቁጥር 9/2003 ንዑስ ቁጥር 12/ለ፣ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች አዲስ ስቶክ ሲቀበሉ በሚከተሉት ላይ ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ይኖርባቸዋል በሚለው ስር «የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) ጋር በማመሣከር ወይም ባለሙያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሙያ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ማግኘት» እንዳለባቸው፣ እንዲሁም በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 1 ቁጥር 9.2 እና 9.4 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ስር «ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (specification) መሠረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መስጠቱንና አስፈላጊ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመስጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ» እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም፣

   - የዩኒቨርሲቲው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በዱቤ የገዛቸው መድሃኒቶች በመድኃኒቶቹ ባህሪያት ዝርዝር (Specifications) መሰረት ለመቅረባቸው በቴክኒክ ኮሚቴ /Technical committee/ ሳይረጋገጥ ገቢ ለተደረጉ መድኃኒቶች ብር 4,041,459.83 የተከፈለ መሆኑ፣
   - ኮሌጁ ከላይ ለተመለከተው በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ከኤጀንሲው ለገዛው መድሃኒት ክፍያ በፈጸመበት ወቅት ለብር 2,873,129.51 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልተቀበለ እና ሂሳቡ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

5. በውስን ጨረታ የሚገዛው ዕቃ ዋጋ ከብር 1,500,000.00 መብለጥ እንደሌለበት በመመሪያ የተጠቀሰ ቢሆንም ለተማሪዎች ምርቃት የሚውል ጋወን፤ ኮፊያ እና ሪቫን ግዢ በሚል

በመመሪያው ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን /Threshold/ በላይ ብር 1,554,570.00 (በመመሪያው ከታዘዘው በላይ ብር 54,570.00 ተጨምሮበት) መከፈሉ፣

6. እስከበጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ብር 59,714.65 ተሰብሳቢ እና ብር 2,641,745.24 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣
7. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 24 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በሚለው ስር የተፈቀደ በጀት መኖሩ ሳይረጋገጥ ከተፈቀደለት በጀት በላይ ወጪ ማድረግ ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል የተመለከተ ቢሆንም፣ ለዩኒቨርሲቲው በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደለት የተስተካከለ በጀትና በስራ ላይ የዋለው ሂሳብ በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ለየሂሳብ መደቦቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ብር 8,892,518.40 ተገኝቷል፡፡
8. በግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ላይ ለውስን ጨረታ ግዥ ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ውጤታማ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ እስከተቻለ ድረስ የተወዳዳሪዎቹ ቁጥር ከ5 /አምስት/ ማነስ እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲው በ2009 ዓ.ም ምረቃ በዓል የሚውል የድንኳን አገልግሎት ኪራይ እና ዲኮሬሽን አገልግሎት ለማሰራት በውስን ጨረታ 3 ዕጩ ተወዳደሪዎችን ብቻ በማወዳደር ብር 378,801.15 ወጪ ማድረጉ፣
9. የገቢና የወጪ ሂሳቦች የተያዙትና የተመዘገቡት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 1,227,398.00 የትርፍ ሰዓት /Overload/ ክፍያ በሂሳብ መደብ 6116 (ለቋሚ ሰራተኞች አበል በሚለው) መመዝገብ እና ሪፖርት መደረግ ሲገባ በሂሳብ መደብ 6251 (በውል የሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎቶች) ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ ሲሆን በበጀት አርእስት 6116 ከላይ የተገለጸው የገንዘብ መጠን ሳይካተት ከበጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑን በበጀት ማነጻጸሪያ ላይ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1. **ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)**

- በዩኒቨርሲቲው ግብርና ካምፓስ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች በተለይ በዋጋ ማወዳደሪያ በተገዛበት ወቅት አሸናፊው ድርጅት ያቀረበው ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑ መረጋገጥ ሲገባው፣ በበጀት ዓመቱ በናሙና በታዩት በዋጋ ማቅረቢያ የግዢ ዘዴ ለተገዙት ዕቃዎች ተገቢው የገበያ ጥናት ሪፖርት ሳይቀርብ በድምሩ ብር 297,720.00 ለተለያዩ ሁለት ድርጅቶች መከፈሉ፣
- አፍሮ ፂዮን ኮንስትራክሽ ለተለያዩ የግንባታ ስራዎች በቀን 28/08/2008 (06/05/16) ተጀምረው በቀን 26/08/2010 (04/05/18) ይጠናቀቃል ተብለው በብር 881,787,388.10 ውለታ ከተገባባቸው ሥራዎች ውስጥ በብር 98,395,265.00 ውለታ የተገባበት የሳይት ወርክ ሥራ (የአዲሱ ዋናው ግቢ የአስፋልት ሥራ) እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 14.73% ላይ የሚገኝ መሆኑ
- ከመደበኛ በጀት በየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ ያልተሰራበት በጀት ብር 3,207,627.81 መኖሩ፣

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

- ከዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሶስት ገንዘብ ያዦች ውስጥ ብዙነሽ መኩሪያ የተባሉ ረዳት ገንዘብ ያዥ ከሂሳብ ክፍል ሰራተኞች ጋር በአንድ ቢሮ የሚሰሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ቢሮው የካዝና የደህንነት መከላከያ ፍርግርግ /Grill/ የሌለው መሆኑ እና በተጨማሪም በረዳት ገንዘብ ያዧ ስም በሚጠበቀው ሳጥን /ካዝና/ ውስጥ ሰኔ 30/2009 ገንዘብ እንዳለ ወይም እንደሌለ እና ካለ ስንት እንደሆነ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣

ንብረት፤

- በዋናው ካምፓስ የአዲስና የተመላሽ የቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት ሠራተኛ ንብረት የመረከብ እና የገቢና ወጪ ደረሰኞች (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀት ሥራዎችን የሚያከናውኑ፣ በተጨማሪም የገቢና የወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ የሌለ መሆኑ፤
- ከሱቢ የጽህፈት መሳሪያና የቢሮ ዕቃዎች አቅራቢ ጋር የብር 811,998.00 ዋጋ ያላቸው 5 የተለያዩ ፈርኒቸሮች እንዲቀርብ በ22/05/2009 ውል የተገባ ሲሆን፣ ውለታ ከተገባባቸው 5 ዓይነት ቢሮ ዕቃዎች ሃይባክ ማኔጂሪያል ተሽርካሪ ወንበሮች ብዛት 80 እና የሴክሬታሪ

ተሽከርካሪ ወንበሮች ብዛት 80፣ በድምሩ የብር 255,999.20 ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች አቅርቦ በጥራት ጉድለት ምክንያት ዕቃዎቹ ተመላሽ የተደረጉ ከመሆኑም በተጨማሪ ብር 159,999.96 ዋጋ ካላቸው ብዛት 80 የቢሮ ጠረጴዛዎች ውስጥ 35 (43.75%) የሚሆኑት ጭራሽ ሣይገጠሙ ብረቶቻቸው በዋናው ግቢ ውስጥ ጸሃይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ያሉትን ጨምሮ የጥራት አረጋጋጭም በውለታው መሠረት የቀረቡ መሆኑን ባረጋገጠው መሰረት ሥራቸው ሳይጠናቀቅ (ሳይገጠሙ) በ23/09/09 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 824102 ተዘጋጅቶላቸው በውለታው መሰረት ላልቀረቡ ወንበሮች ለአቅራቢው አላግባብ ብር 69,999.65 (35*1999.99) የተከፈለ መሆኑ፤

- በዋናው ካምፓስ የአዲስና የተመላሽ የቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት ሠራተኛው ከቀድሞ የግምጃ ቤት ሠራተኛ ምንም ዓይነት ርክክብ ያልተፈጸመባቸው በአቅራቢዎች ለናሙና የቀረቡ እንደ ብርድልብስ፣ ሽሚዞች፣ የዝናብ ልብሶች፣ ስፖንጅ ፍራሾች ያሉ የተለያዩ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፤
- በዋናው ካምፓስና በግብርና ኮሌጅ ግቢ በ3 የቆርቆሮ ግምጃ ቤቶች እጅግ በጣም ብዛት ያላቸው ያልተጠገኑና ተጠግናው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የተማሪዎች የብረት አልጋ ያለምንም እርምጀ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በዋናው ካምፓስና በግብርና ኮሌጅ በቆርቆሮ ግምጃ ቤቶች በርካታ አሮጌ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ክሊነሮች፣ ፕሮጀክተሮች (LCD)፣ የተለያዩ የላብራቶር ዕቃዎች፣ ያመሃ ሞተር ብስክሌት የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 4-0784 ኦሮ ለዓመታት በአሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት የተቀመጠ፣ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች፣ የተለያዩ የኤሌክሮኒክስ ዕቃዎችና ሌሎች የተለያዩ ንብረቶች በየግምጃ ቤቶቹ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በዋናው ካምፓስ በኑሩ ሀሚድ የህንጻ መሳሪያ መደብር የቀረቡና በጥራት ችግር ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ያልተረከባቸው የተባሉ ሞራሌ ያለምንም እርምጃ በግቢ ውስጥ ጸሃይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው መሆኑ፤
- በግብርና ኮሌጅ የቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት የተማሪዎች ዶርም በገነባው ጭላሎ ኮንስትራክሽን ከ2 ዓመት በፊት በአደራ የተቀመጡ 12 አነስተኛ እሳት አደጋ መከላከዎች፣ እንዲሁም 4 ትልልቅ የእሳት አደጋ መከላከያዎች ደግሞ በንብረትነት የተመዘገቡ በዩኒቨርስቲው የግንባታ ጽ/ቤት ሃላፊ የቃል ትዕዛዝ የተቀመጡ በህንጻዎቹ ላይ መተከል (መገጠም) ሲገባው ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤

- በICT የሥራ ክፍል ጠያቂነት ተገዛ የተባለ ኬብል ትራክ ብዛት 600 ብር 30,000.00 ዋጋ ያለው ያለአገልግሎት ከ1ዓመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፤

<u>የተማሪዎች ክሊኒክ መድሃኒትና የህክምና አገልግሎት፤</u>

- በግብርና ኮሌጅ፣
  - ➢ ከዚህ ቀደም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ መድሃኒቶች የተወገዱ ቢሆንም አሁንም ዓይነታቸውና ብዛታቸው በዝርዝር ያልተለዩ በመድኃኒት ግምጃ ቤትና በመድኃኒት ማደያ ክፍል (Dispencery Room) የሚገኙ መሆኑ፣
  - ➢ በኮሌጁ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በመድሃኒት ግምጃ ቤት የሚገኙት መድኃቶች ቆጠራ ሲደረግ በመድኃኒት ማደያ የሚገኙት ቆጠራ ያልተቆጠሩ መሆኑ፣
  - ➢ ኮሌጁ መድኃኒትና የህምና ዕቃዎች በቀጥታ ከአሰላ ሪፈራል ሆስፒታል እየጠየቀ በማምጣት በመጠቀም ለሆስፒታሉ ክፍያው እንደሚፈጸም ቢገለጽም ክሊኒኩ በየጊዜው መድሃኒት ሲጠይቅ አስቀድሞ ተጠይቆ ከመጣው በመድኃኒት ግምጃ ቤትና በመድኃኒት ማደያ ያለው ቀሪ ሳይታወቅ ሌላ እየተጠየቀ የሚመጣ መሆኑ፤

<u>የጽህፈትና ሌሎች አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት፤</u>

- በዋናው ካምፓስ የአላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት በኮኪ ሥራ አቅራቢ ድርጅት የቀረቡ ክፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ የተደረገባቸው፤ በካርቶን ቦክሰ ፋል 10፤መዝገብ ትልቅ 16፤ ከለር ወረቀት 10፤ ፕሮቶኮል መዝገብ 7፤ የፕሪንተር ወረቀት 4፤ ፖስታ የተለያየ መጠን ያላቸው 30፤ ሰስፔንሽን ፋይል 30፤ ለዕቃ ርክክብ ያልተፈጸመባቸውና በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ገና ያልታዩ አቅራቢው ካቀረባቸው ከ8 ቀናት በላይ የሆናቸው ንብረቶች ለዕቃ ግምጃ ቤትነት ባልተዘጋጀ ክፍል ውስጥ ለብልሽት በሚዳርግ መለኩ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው በወለል ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በዋናው ካምፓስ ተገዛው መጠን ወዲያውኑ ወጪ የሚደረጉ አላቂ እቃዎች ገቢ እና ወጪያቸው በቢን ካርድና በስቶክ ካርድ ላይ የማይመዘገቡ መሆኑ፤
- ዩኒቨርስቲው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤ የንብረት የገቢና ወጪ (ሞ/19 እና ሞ/22) እንዲሁም የተለያዩ የሂሳብ የወጪ ሰነዶችን ኮሌጆች ከዋናው ካምፓስ እንዲወስዱ ሲደረግ (መውሰድ ሲጀምሩ) አስቀድሞ ኮሌጆቹ በአዳማ ዩኒቨርስቲ ሥር በነበሩበት ወቅት የወሰዱአቸው፣ በተለይ ያልተሰራባቸው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤ የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች እንዲሁም የተለያዩ የሂሳብ የወጪ ሰነዶች ርክክብ ሳይፈጸም በሠራተኞቹ እጅ የሚገኙ መሆኑ፤

<u>የተማሪዎች ምግብ ግብዓቶችና ሌሎች ዕቃዎች፤</u>

- በየዕለቱ ከአቅራቢው (ሣጉሬ ዳቦ ቤት) ለዋናው ግቢ የሚቀርበው ዳቦ የግምጃ ቤት ሠራተኛዋ ያለምንም ታዛቢና የጥራት አረጋጋጭ በቀጥታ ከአቅራቢው የሚረከቡ ከመሆኑም በተጨማሪ የሚቀርበው ዳቦ በውለታው መሰረት መጠኑን (ግራሙን) ጠብቆ እየቀረበ መሆኑን በናሙና እንኳ እየተመዘነ የማይረጋገጥ መሆኑ፤
- ከጤፍ አቅራቢዋ (ሙሁዋባ) ከውለታ በፊት (ውለታ ሳይገባ) 2 ቀን (በ5/08/09 እና 7/08/09) ከቀረቡትና በጥራት አረጋጋጭም ተረጋግጦ ካለፈው 138.58 (64.94+73.64) ኩንታል ጤፍ ውሰጥ፣
    - ➢ 105 ኩንታሉ ጥራቱን ያልጠበቀ (ቀጭ ቀጭ ያለው) መሆኑ እየታወቀ ከሌላ ጤፍ ጋር በ20/09/2009 የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ቁጥር 494756 ተዘጋጅቶለት አላግባብ ብር 249,795.00 (105*2379) ለአቅራቢዋ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ (በንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 494756 ገቢ ከተደረገው ብር 593,275.02 ውስጥ)
    - ➢ ከላይ ከተጠቀሰው ጥራቱን ያልጠበቀ 105 ኩንታል ጤፍ ውስጥ 75 ኩንታሉ በጤፍ ግምጃ ቤት፣ 30 ኩንታሉ ደግሞ በሚኒስቶር ያለምንም እርምጃ የተቀመጠ ከመሆኑም በተጨማሪ በተበላሸው ጤፍ ላይ እርምጃ ሳይወሰድ አቅራቢዋ አሁንም ጤፍ እያቀረቡ መሆኑ፤
    - ➢ ከአቅራቢዋ ጋር በ20/08/09 የተገባው ውለታ ከ29/12/08-28/12/09 (ለ1ዓመት)እንደገባ ተደርጎ ካቋረጠው አቅራቢ የተገባውን የውለታ ጊዜ በመጠቀም ውለታ የተገባ መሆኑ፤ (ቀጭ ቀጭ ጤፉ አስቀድሞ በነበረው አቅራቢ እንደቀረበ አሊያም አቅራቢዋ አስቀድሞም ታቀርብ እንደነበረ ለማድረግ የተደረገ መሆኑ)
- ለግብርና ኮሌጅ ተማሪዎች ቀለብ አስቀድሞ ጤፍ ለማቅረብ ከ29/12/08-28/12/09 (ለ1ዓመት) ውለታ የገባው ከበበ ለሜሣ የብዕርና የአገዳ ሰብሎች አቅራቢ ውለታውን ሲያቋርጥ በዩኒቨርሲቲው ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- በምግብ ዕቃዎች ሚኒ ስቶር ወስጥ በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የተቀመጡ (የማይሰሩ) 2 ፍሪጆች፤ በኩዊታል በውጭ የተከመረ ብዛት ያለው የጤፍ ብጣሪ ያለምንም እርምጃ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በግልጽ ጨረታ ተወዳድረው በአሸናፊነት የተመረጡ የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃና ማጣፈጫዎች አቅራቢዎች የሚያቀርቡአቸው ዕቃዎች የጥራት ማነስ (ጉድለት) በሚታይባቸው አቅራቢዎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ በዕቃው ተጠቃሚ ክፍሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የበላይ ሃላፊዎች በጽሁፍ ሪፖርት የሚደረግ ቢሆንም ሪፖርት የተደረገለት አካል ሁኔታውን አጣርቶ

እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፤ (ለናሙና፤ ከተማሪዎች ጉዳይ ቡድን መሪ በ01/10/09 በተጻፈ ደብዳቤ ድንች፤ጥቅል ጎመን፤ የምግብ ጨው፤ ቃሪያና ቀይ ሽንኩርት አቅራቢዎች የሚያቀርቡት ዕቃ ጥራቱን ያልጠበቀ መሆኑ ተማሪዎች ጉዳይ ተ/ዲን ሪፖርት የተደረገ)፣ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>ተሽከርካሪ መኪናዎች</u>

- ዩኒቨርሲቲው ካሉት 66 ተሽከርካሪዎች ውስጥ፤ 18 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፤ የ8 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ መቁጠሪያ (ጌጅ) የማይሰራ መሆኑ፤ 48 ተሽከርካሪዎች ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት /ኖርማላይዜሽን/ ያልተሰራላቸው /የሌላቸው/ መሆኑ፣

<u>ዩኒቨርሲቲው ለመኖሪያነት የተከራያቸው ቤቶችን በተመለከተ፣</u>

- ዩኒቨርስቲው ከ4 ግለሰቦች የተከራያቸው በቁጥር 12 ቤቶችን (1 ህንጻ 9 የተለያዩ ክፍሎች ወይም መኝታዎች የያዘና ሌሎች 3 ቤቶች) በተመለከተ የተጠየቀው ዝርዝር መረጃ ዘግይቶ በ27/10/09 የቀረበ እና ዝርዝር መረጃው 8ቱ (በህንጻው ካሉት 5ቱ እና ለየብቻ ያሉት 3ቱ) ለተጠቃሚዎች መተላለፋቸውን የሚያመለክት ቢሆንም ከዩኒቨርሲቲው የገበያ ጥናት ባለሙያ ጋር በመሆን አስቀድሞ በ16/10/09 በተደረገ የመስክ ኦዲት ቅኝት ወቅት በህንጻው ከሚገኙ ቤቶች 6 ቱም ስቱዲዮዎች ለተጠቃሚዎች አለመተላለፋቸው የተረጋገጠ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ቤት ተከራይቶ ከሰጣቸው ተጠቃሚዎች ጋር ውለታ የሌለው መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው በፋሲሊቲ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሥር የመኖሪያ ቤቶችና ስታፍ ላውንጅ የሥራ ክፍል ያለው ቢሆንም የተጠቀሱት በኪራይ የተገኙ ቤቶች ወደ የሚመለከተው የሥራ ክፍል ባለመተላለፋቸው በማን ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው የማይታወቅ መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ከአገልግሎት ሰጪዎች የሚፈጸሙ ውለታዎች ለአገልግሎት ሰጪዎቹ ለክርክርና መንግስትን አግባብ ላልሆነ ወጪ በሚዳርግ መልኩ የሚዘጋጁ መሆኑ፤

<u>የመምህራንና ሠራተኞች መኖሪያ ቤቶችን በተመለከተ፣</u>

- ከተጠቀሱት በተለያየ ሳይት ከሚገኙ የተለያየ ደረጃ ያላቸው ቤቶች ውስጥ በበቆጂ 27፤ በግብርና 10፤ በዲንሾ ኮንዶሚኒየም 23፣ በድምሩ 60 ቤቶች ለጠተቃሚዎች ያልተላለፉ መሆኑ፣
- ዲንሾ ሳይት ከሚገኙ 2 ክሎክ የኮንዶሚኒየም 67 የተለያየ ደረጃ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ውሰጥ፤

- ➢ ለተጠቃሚዎች ያልተላለፉ ቤቶች 8 ባለ 1፤ 1 ባለ 3፤ 10 ስቱዲዮ፣ በጠቅላላው 19 ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ ካለመሆኑም በተጨማሪ ከተጠቀሱት ቤቶች ውስጥ 4 ስቱዲዮዎች ወደ 2 ለመለወጥ (ለማስፋት) መሃላቸው የፈረሰና ያልተሰሩ መሆኑ፣
- ➢ ባለ 1 መኝታ ቤት የተሰጣቸው ተጠቃሚ (መምህር ሰይድ የሱፍ) ያለምንም የተቋሙ እውቅና (ጉዳዩ የሚመለከተው የሥራ ክፍል) ለሌላ ሰው (ለዩኒቨርሲቲው የስራ ባልደረባ ላልሆኑት) ሰጥተውት የሚኖርበት መሆኑ፣

- በግብርና ሳይት ከሚገኙ 121 የተለያዩ ቤቶች ውስጥ 10 ዶርሞች ለተጠቃሚዎች ያልተላለፉ መሆኑ፣
- በቆጂ ከሚገኙ ለተጠቃሚዎች ካልተላለፉት 27 ቤቶች ውስጥ 5ቱ በህጋዊነት የተሰጣቸው ለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበና ምንም ዓይነት ውለታ በሌላቸው የኮሌጁ ሠራተኞች የተያዙ ከመሆኑም በተጨማሪ በመኖሪያዎቹ ግቢ ውስጥ የዩኒቨርሲው አካል ያልሆነ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የሙብራት ሃይል የኮንክሪት ፖል የሚያመርት ሲሆን ይህ በማን እንደተፈቀደ የማይታወቅ መሆኑ፣
- ዩኒቨርስቲው ከበቆጂ ከተማ አስተዳደር ያለ ማስረጃ በስጦታ የተረከባቸው የተለያየ ደረጃ ያላቸው 31 ቤቶች ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ ጥገና የተደረገላቸው ቢሆንም በአብዛኛው (27ቱ ወይም 88%) አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ከመሆኑም በተጨማሪ ጥገና የተደረገላቸው ከተባሉት ቤቶች ውስጥ ጭራሽ በር የሌላቸው የሚገኙ መሆኑ፤ (ለናሙና፤ በር ስለሌለው እንስሳት የሚያድሩበት 1 ስቱድዮ ቤት፤ ለ14ቱ ቤቶች የሚያገለግል ሻወር ቤትና ማጠቢያ ክፍል በር ስለሌለው የቆሻሻ አሮጌ ዕቃ ማከማቻ መሆናቸው)
- በበቆጂ ከሚገኙት ለተጠቃሚዎች ከተሰጡ ቤቶች 4ቱ (2 ባለ ሁለት መኝታና 2 ደግሞ ባለአንድ መኝታ ቤቶች) አስቀድሞ ዩኒቨርስቲው ከመቋቋሙ በፊት የተሰጣቸው የሶሻል ሳይንስና የሂዩማኒቲ ኮሌጁ መምህራን በዩኒቨርስቲው ሥር ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ከ2 ዓመት በላይ በየወሩ የሚከፈላቸው የቤት አበል መቋረጥ ሲገባው አላግባብ በድጋሚ ለ4ቱም መምህራን በበጀት ዓመቱ ከሀምሌ 1/08 - መጋቢት 30/09 (ለ9 ወራት) ብር 30,600.00 (800*9*3 + 1000*9*1) ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- 156 ለተጠቃሚዎች ከተላለፉ ቤቶች ውስጥ የተለያየ ደረጃ ያላቸው ብዛታቸው 11 የሚሆኑት በአስተዳደር ዘርፍ ለሚገኙ ሠራተኞች በኪራይ የተሰጡ ከመሆኑም በተጨማሪ የኪራይ ውል የሌላቸው መሆኑ፤ (4 ዶርሞች በብር 35.00፤ 2 ስቱዲዮ በብር 50.00፤ 3 ባለ

1 መኝታዎች በተለያየ ዋጋ አንዱ በብር 50.00 እና 2ቱ እያንዳንዳቸው በብር 100.00፤ 1 ባለ 2 መኝታ ቤቶች በብር 200.00)

- 1 ባለ2 መኝታ፤ 4 ባለ 1መኝታ፤ 6 ዶርሞችና ስቱዲዩ ቤቶች መምህራኑ የማይፈልጉአቸው መሆኑን ሳይረጋገጥ በአስተዳደር ሥራ ላይ ለተመደቡት የተሰጡ መሆኑ፣
- በ23/10/09 በተደረገ የመስክ ኦዲት ቅኝት ወቅት በግብርና ሳይት የሚገኙት ቤቶች የአብዘኞቹ ወደ ግቢ ለመግባት በማያስችል መልኩ በሳርና አረም የተከበበ፤ በዲንሾ ሳይት ደግሞ በተለይ አንዱ ብሎክ (ከመግቢያ በር አጠገብ ያለው) በየበረንዳው የተቀመጡ አርጌ ዕቃዎች፤ በመወጣጫው ግራና ቀኝ የተለያየ ቆሻሻ ነዋሪ ያለበት በማይመስል መልኩ የጽዳት ጉድለት የሚታይባቸው መሆኑ፣

<u>እርምጃ ያልተወሰደበት የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ከዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፤ ከጤና ሳይንስ ኮሌጅ መጻህፍት በትውስት ወስደው ለዓመታት ያልመለሱ መምህራንና ሠራተኞች መጽሃፍቱን እንዲመልሱ በላይብረሪ ዳይሬክቶሬቱ በኩል ተደጋጋሚ ጥረት ተደርጎ ንብረቱ የሚፈለግባቸው መምሀራንና ሠራተኞች ሊመልሱ ባለመቻላቸው ጉዳዩን ለውስጥ ኦዲት በማሳወቅ የውስጥ ኦዲት ክፍሉም እርምጃ እንዲወሰድ ለዩኒቨርሲቲው ሪፖርት ቢያደርግም በሥራ አመራሩ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአርሲ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፡-

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአርሲ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፡-

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲውን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት ፡-

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በአርሲ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የአርሲ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **<u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፤</u>**

1.1 **<u>ግኝት፤</u>**

የፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 3 የካዝና ቁልፍ እና የሚቀመጥበት ሁኔታ በሚለው ስር «የመንግሥት ካዝና የሚቀመጥበት ክፍል ከገንዘብ ያዡ በስተቀር ሌላ ሠራተኛ በጋራ ሊገለገልበት የማይችል መሆን እንዳለበት» የተመለከተ ቢሆንም፤

- ከዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሶስት ገንዘብ ያዦች ውስጥ ብዙነሽ መኩሪያ የተባሉ ረዳት ገንዘብ ያዥ ከሂሳብ ክፍል ሰራተኞች ጋር በአንድ ቢሮ የሚሰሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ቢሮው የካዝና የደህንነት መከላከያ ፍርግርግ /Grill/ የሌለው መሆኑ፤
- በተጨማሪም በረዳት ገንዘብ ያዧ ስም በሚጠበቀው ሳጥን /ካዝና/ ውስጥ ሰኔ 30/2009 ገንዘብ እንዳለ ወይም እንደሌለ እና ካለ ስንት እንደሆነ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

1.2 <u>ስጋት፣</u>

- በጋራ ቢሮ ውስጥ ገንዘብ እንዲጠበቅ ማድረግ ገንዘብ ቢጠፋ /ቢጎድል/ተጠያቂው ማን እንደሆነ በቀላሉ ለመለየት አያስችልም፡፡
- ገንዘብ ለሚቀመጥበት ቢሮ የካዝና የደህንነት መከላከያ ፍርግርግ /Grill/ አለመኖር የመንግስት ገንዘብ በቀላሉ ለስርቆት እንዲጋለጥ በር ይከፍታል፡፡

1.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

በጋራ ቢሮ ገንዘብ እንዳይቀመጥ እና የጥሬ ገንዘብ ሳጥን የሚቀመጥበት ክፍል ተገቢው ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡

1.4 **<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>**

- ዩኒቨርሲቲው አዲስ ከመሆኑ የተነሳ የተሟላ መሠረተ ልማት የሌለው ስለሆነ ግንባታው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ቢሮዎችን የተለያዩ ሥራ ክፍሎች /share/ በማድረግ እንዲጠቀሙ አስገድዷል፡፡
    - ዩኒቨርስቲው አዲስ በመሆኑ የተነሳ የተሟላ ቢሮ ባለመኖሩ ሠራተኞች ቢሮዎችን በመጋራት እንዲሰሩ በመገደዳቸው መሆኑን ጠቅሰው ለደህንነቱ ዕለታዊ የሳጥን ገንዘብ ቆጠራ እንደሚደረግ እና

- ሰኔ 30/ 2009 ዓ.ም በረዳት ገንዘብ ያዥዋ ዕጅ ገንዘብ ባለመኖሩ ፎርሙ ላይ አለመሞላቱ ክፍተት መሆኑን ጠቅሰው ትምህርት እንደወሰዱበት ገልጸዋል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

2.1 <u>ያልተሰበሰበ የህክምና ዱቤ ሽያጭ ገቢ</u>፣

2.1.1 <u>ግኝት፤</u>

በአርሲ ዩኒቨርሲቲ አሰላ ሆስፒታል የአገልግሎትና የመድኃኒት ሽያጭ ገቢ ደንብና መመሪያን ተከትሎ የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከሀምሌ 1/2008 ጀምሮ ከሆስፒታሉ በዱቤ ሽያጭ አገልግሎት ካገኙ ሰባት /7/ ተቋማት መሰብሰብ የሚገባው ብር 160,795.60 ሂሳብ ሳይሰብሰብ የተገኘ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	የዱቤ ተጠቃሚው ድርጅቶች ስም	የገንዘቡ ልክ
1	ዲጋሉና ጢጆ ወረዳ ጤና ኢንሹራንስ	57,704.28
2	ሙኔሳ ወረዳ ጤና ኢንሹራንስ	37,764.05
3	ሂጦሳ ወረዳ	48,811.14
4	ዝዋይ ዱግዳ ወረዳ	1,755.31
5	የመብራት ሃይል ሰራተኞች /ሳጉሬ/	1,810.50
6	ጢዮ ወረዳ	9,300.84
7	ኦሮሚያ ምርጥ ዘር	3,649.30
	ድምር	**160,795.42**

2.1.2 <u>*ሥጋት*</u>፣

የዱቤ ህክምና ገቢ በወቅቱ አለመሰብሰብ ከቆይታ ብዛት ወደ ማይሰበሰብበት ደረጃ ሊያደርስ የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ አግባብ ያልሆኑ ወጪዎች ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ያልተሰበሰበው የዱቤ ሽያጭ ህክምና ገቢ ሂሳብ በወቅቱ ተሰብስቦ ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሆኔታ እንዳይከሰት በዱቤ ህክምና አገልግሎት ላይ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፤

የሥራ አመራሩ ሂሳቡ በመሰብሰብ ላይ መሆኑን በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>፣

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት መዋሉን፤ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙን፣ የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን፣ እንዲሁም ለታቀደለት ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1 <u>የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ የተፈጸመ ጊዜያዊ ቅጥር</u>፣

3.1.1 <u>ግኝት</u>፣

ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 ዓ.ም በተላለፈ መመሪያ መሰረት ‹‹በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተለመደና ዘላቂነት በሌለው የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሰራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ በኮንትራት/በጊዜያዊነት/ ቅጥር እንደማይፈጸም›› በመመሪያው የተመለከተ ቢሆንም፣ በዩኒቨርሲቲው ዋናው ካምፓስ የነፃ የህግ አገልግሎት ለሰጡ የአስተዳደር ሰራተኞች ጊዜያዊ /ኮንትራት/ ቅጥር ለመፈፀም በቅድሚያ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴርን ማስፈቀድ ሲገባ፤ ዘላቂነት ላለው የስራ መደብ ከሚኒስቴሩ ፍቃድ ውጭ 11 ለሚሆኑ የአስተዳደር ሰራተኞች በኮንትራት ቅጥር በመፈፀሙ፤ በበጀት ዓመቱ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ በሚል በናሙና በታየው መሰረት በድምሩ ብር 69,766.68 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ተመልክቷል፡፡)

3.1.2 <u>ስጋት</u>፤

ክፍያዎችን ከደንብና መመሪያ ውጪ መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

3.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፤

- በማንኛውም የፌዴራል መንግስት መ/ቤት እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት /ጊዜያዊ/ ቅጥር ለመፈፀም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በቅድሚያ ለሚኒሰቴሩ (ፐብሊክ ሰርቪስ ሚ/ር) እየቀረበ ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ አለበት፡፡

- ዘላቂነት ባለው የስራ መደብ ላይ የኮንትራት ሰራተኞችን መቅጠር መመሪያውን ያልተከተለ በመሆኑ ሰራተኞቹ ወደ ቋሚነት የሚዞሩበት አግባብ እስኪመቻች ድረስ የሚከፈለው የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ እንዲቋረጥ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም ስራ አመራሩ በኦዲት ግኝት ወቅት የሚሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦችን በመመርኮዝ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ ቀደም ሲል ከሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በተሰጠ ድጋፍ የነፃ ህግ ሰራተኛ ደመወዝ ሲከፈል የቆየ ቢሆንም በድንገት ድጋፍ በመቋረጡ ስራው አስፈላጊ ስለነበረ የህዝብ ጥያቄም በመቅረቡ ዘላቂ መፍትሄ እስከሚገኝ ከመደበኛ ደመወዝ ሊከፈል መቻሉን ገልጸው አሁን ግን ሠራተኞቹም መቀነሳቸውን እና ፈንድ በማፈላለግ ላይ መሆናቸውን ገጸዋል፡፡

3.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ከፍ ሲል ቀንና ቁጥሩ በተጠቀሰው መመሪያ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት የተጠቀሰ በመሆኑ ለወደፊቱ በመመሪያው መሠረት መሠራት አለበት፡፡

3.2 በመንግሥት የወጣ ተመን ሳይኖረው በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ውሳኔ የተፈጸመ የ Professional Fee ክፍያ፣

3.2.1 ግኝት፣

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በ13/8/03 በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ‹‹ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሠራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ›› የታዘዘ እና በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሌጂስሌሽን ደግሞ የአካዳሚክ ባለሙያዎች ግዴታዎች በሚለው ስር ተማሪዎችን ማማከር፤ ፈተና መፈተን፤ የማስተማሪያ መሳሪያ መከለስ እና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም፣

- ክፍያው በሴኔት ቋሚ ኮሚቴ ለመወሰኑ ተጠቅሶ በ4/12/08 በቁጥር 1-2/02/1498/98 ከአካዳሚክ ም/ፕረዝዳንት ለዩኒቨርሲቲው ፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በተጻፈው

መሠረት ለዩኒቨርሲቲው በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የማማከር አገልግሎት /Thesis Advise/ ለሰጡ ሰባት አካደሚክ ባለሙያዎች በብር 4,320.00 ተመን፤ የፈተና አገልግሎት /Internal and External Examiners/ ለሰጡ 15 አካደሚክ ባለሙያዎች በብር 1,500.00 ተመን እና Thesis Chairperson እና proposal review አገልግሎት ለሰጡ 6 አካደሚክ ባለሙያዎች በብር 750.00 ተመን፣ በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 240,750.00 በመንግሥት የተፈቀደ ተመን ሳይኖር በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ውሳኔ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 2 ተመልክቷል፡፡)

3.2.2 <u>ስጋት፡</u>

የመንግስት ውስን በጀት ከታለመለት ዓላማ ውጪ እንዲውል መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

3.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

- ክፍያዎች ከመፈጸማቸዉ በፊት የክፍያዎቹ ህጋዊነትና አግባቢነት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የክፍያዎቹ አስፈላጊነት ከታመነበትም የሚመለከተዉን አካል አስፈቅዶ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የስራ አመራሩ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

3.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ ፤</u>

የሥራ አመራሩ በዩኒቨርስቲው በሴኔት ሌጅስሌሽን መመሪያ መሰረት የተከፈለ መሆኑን፣ በሌሎች ዩኒቨርስቲዎችም ተመሳሳይ ክፍያዎች መኖራቸውን እና ወጥነት ያለው መመሪያ አንደ ሀገር ካልተቀረፀ በስተቀር ሙያተኞች ወደ ዩኒቨርስቲው መጥተው ሥራ ለመስራት አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠርብናል የሚል ስጋት እንዳለባቸው ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

3.3 <u>በትርፍ ሰዓት ላስተማሩ በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ፣</u>

3.3.1 <u>ግኝት፣</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ሚያዚያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም በቁጥር ት/ሚ.259/82-18/03 የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ማብራሪያ በሚለው ስር ‹‹ከስራው ዓለም በጊዜያዊ ቅጥር (part time) የሚሰማሩ ካሉም ለሙሉ፤ ለተጠባባቂ እና ረዳት ፕሮፌሰር ብር 120.00፤ ለሌክቸረር ብር 100.00፤ ረ/ሌክቸር እና ምሩቅ ብር 65.00፤ እና ለቴክኒክ ረዳት

ብር 45.00 በዚሁ ተመን ስሌት ብቻ እንደሚከፈላቸው›› የተመለከተ ቢሆንም፣ በዩኒቨርሲቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በእንግዳ /በተጋባዥ/ መምህርነት የትርፍ ሰዓት /Over load/ ላስተማሩ የጤና ባለሙያዎች በክሬዲት ሃዎር /Cr.Hr/ ብር 120.00 ታስቦ በድምሩ ብር 80,640.00 መከፈል ሲገባ በክሬዲት ሃዎር /Cr.Hr/ ብር 200.00 በማሰብ በ12/04/09 በሂሳብ ምዝገባ ቁጥር 49651 በድምሩ ብር 134,400.00 ለ4 ተጋባዥ መምህራን በመከፈሉ በልዩነት /በብልጫ/ በድምሩ ብር 53,760.00 የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3.3.2 <u>ስጋት፡</u>

መንግስት ባወጣው የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተመን መሰረት የማይከናወን ከሆን የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.3.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

- ኮሌጁ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ክፍያ ሲፈፅም /ሲከፍል/ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ ያለአግባብ ጭማሪ በማድረግ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሆኖ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡
- ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ለሚመለከተው አካል በጥብቅ ማስገንዘብ ይገባል፡፡

3.3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ በዩኒቨርስቲው በሴኔት ሌጀስትሬሽን መመሪያ መሰረት የተከፈለ መሆኑን፣ በሌሎች ዩኒቨርስቲዎችም ተመሳሳይ ክፍያዎች መኖራቸውን እና ወጥነት ያለው መመሪያ አንደ ሀገር ካልተቀረፀ በስተቀር ሙያተኞች ወደ ዩኒቨርስቲው መጥተው ሥራ ለመስራት አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠርብናል የሚል ስጋት እንዳለባቸው ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

3.4 <u>የመድሃኒት ግዢን በተመለከተ፣</u>

3.4.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪ□ ቁጥር 9/2003 ንዑስ ቁጥር 12/ለ፣ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች አዲስ ስቶክ ሲቀበሉ በሚከተሉት ላይ ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ይኖርባቸዋል በሚለው ስር «የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) ጋር በማመሣከር ወይም ባለሙያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሙያ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ማግኘት» እንዳለባቸው፣ እንዲሁም በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 1 ቁጥር 9.2 እና 9.4 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ስር «ዕቃው ወይም አገልግሎቱ

በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (specification) መሠረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መስጠቱንና አስፈላጊ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ» እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም፣

- የዩኒቨርሲቲው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በዱቤ የገዛቸው መድሃኒቶች በመድኃኒቶቹ ባህሪያት ዝርዝር (Specifications) መሰረት ለመቅረባቸው በቴክኒክ ኮሚቴ /Technical committee/ ሳይረጋገጥ ገቢ ለተደረጉ መድኃኒቶች ብር 4,041,459.83 የተከፈለ መሆኑ፣
- ኮሌጁ ከላይ ለተመለከተው በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ከኤጀንሲው ለገዛው መድሃኒት ክፍያ በፈጸመበት ወቅት ለብር 2,873,129.51 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልተቀበለ እና ሂሳቡ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ብቻ የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

  (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 3 ተመልክቷል፡፡)

3.4.2 <u>ስጋት፣</u>

- መድኃኒቶቹ ጥራታቸው የተጠበቀና በ(Specifications) መሰረት መቅረባቸው በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ገቢ መደረጋቸው በኮሌጁ ጥያቄ መሰረት የቀረቡ (ገቢ የተደረጉ) መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡
- በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ክፍያ መፈፀምም ለድጋሚ ወጪ የሚጋብዛ አሰራር ነው፡፡

3.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ገቢ የተደረጉ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ የተደረገባቸው መድሃኒቶች በኮሌጁ ፍላጎትና በዕቃዎቹ ባህሪያት ዝርዝር (Specifications) መሰረት የቀረቡና ገቢ የተደረጉ መሆኑ ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ ሊወሰድ እና በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ወጪ ለተደረገው ሂሳብም የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሊቀርብለት ይገባል፡፡
- አሰራሩ ከኮሌጁ ፍላጎት (ትዕዛዝ) ውጪ የሆኑ ዕቃዎች እንዲቀርቡ የሚያደርግና መንግስትን ለድጋሚ ወጪ የሚጋብዝ በመሆኑ ለወደፊቱ ኮሌጁ መመሪያውን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.4.4 **የሥራ አመራሩ ምለሽ፤**

የሥራ አመራሩ፣

- የጥራት አረጋገጫጭ ኮሚቴ ሳይመለከተው ገቢ ተደርገ የተባለው በወቅቱ የተቋቋመ ኮሚቴ ባለመኖሩና የመድሃኒቱ ግዥ በሙያተኛ የተገዛ በመሆኑ መሆኑን ጠቅሰው አሁን Techinical committee መቋቋሙን፣
- በዱቤ ሽያጭ ሂሳቡ ተወራረደ የሚባለው ግዥው የተገዛው ከመድሃኒት ፈንድ ኤጀንሲ መሆኑን፣ በወቅቱ ህጋዊ ደረሰኝ ስላልነበራቸው አለመቀባላቸውን እና ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ አሁን የሰጡአቸውን ማረጋገጫ ደብዳቤ በአባሪነት መያያዛቸውን፣ ወደፊት ግን በዱቤ ሽያጭ ሂሳቡን እንደማያወራርዱ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.4.5 **የኦዲተሩ አስተያየት፣**

- የጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴው የተቋቋመው ከኦዲቱ መውጫ (14/02/2010) በኋላ በ29/02/2010 ቢሆንም ወደፊት ሥራውን በንቃት (actively) ሊተገብር ይገባል፡፡
- በዱቤ ሽያጭ የተወራረደው ሂሳብ ወደ መድሃኒት ፈንድ ኤጀንሲ አዳማ ቅርንጫፍ ባንክ ሂሳብ ገቢ ለመደረጉ ከኤጀንሲው በቀረበው ደብዳቤ የተገለጸው የገንዘብ መጠንም (ብር 4,341,154.77) ከግኝቱ የተለየ በመሆኑ በግኝቱ ለተጠቀሰው መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ስለሆነም በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

3.5 **የገበያ ጥናት ሪፖርት ሳይቀርብ የተፈጸመ ግዥ፣**

3.5.1 **ግኝት፣**

በ2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዢ በሚለው አንቀጽ 24/8 ሥር መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዢዎች በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ-ገፅ የሚወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር፣ በግዢ ሥራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናትን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚኖርበት የተመለከተ ቢሆንም፣ በዩኒቨርሲቲው ግብርና ካምፓስ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች በተለይ በዋጋ ማወዳደሪያ በሚገዛበት ወቅት አሸናፊው ድርጅት ያቀረበው ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑ መረጋገጥ ሲገባው፣ በበጀት ዓመቱ በናሙና በታዩት በዋጋ ማቅረቢያ የግዢ ዘዴ ለተገዙት ዕቃዎች ተገቢው የገበያ ጥናት ሪፖርት ሳይቀርብ፣

- በ19/03/09 በJV ቁጥር 906067 በሂሳብ መደብ 6313 ለላብራቶሪ ዕቃዎች ግዥ ብር 110,720.00፣

- በ08/05/09 በJV ቁጥር 906082 በሂሳብ መደብ 6313 ለሲቢሲ ማሽን ግዢ ብር 187,000፣

በድምሩ ብር 297,720.00 ለተለያዩ ሁለት ድርጅቶች ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.5.2 ስጋት፣

በተለይ በዋጋ ማወዳደሪያ ለሚገዙ ግዢዎች የገበያ ጥናት ሪፖርት አለማቅረብ የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ነው፡፡

3.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የገበያ ዋጋ መሆኑ ሳይረጋገጥ በዋጋ ማወዳደሪያ የግዢ ዘዴ የሚገዛው ዕቃ አሰራሩ እንዲቆምና አላግባብ ለተገዛውም ተገቢው ሪፖርት እንዲቀርብለት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የዩኒቨርሲቲው የግዥ ክፍል በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ-ገፅ የሚወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር በግዢ ስራ ክፍል በሚካሄድ የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን በማረጋገጥ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.5.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ የገበያ ጥናት ሳይቀርብ የተፈፀመ ግዥን በተመለከተ ዩኒቨርስቲው 5 ኮሌጆች ያሉትና አደረጃጀታቸው በተለያየ ርቀት ላይ ስለሚገኙ የሙያተኛ እጥረት እንዳለባቸው፣ ይሁን እንጂ አሁን ተፈፀመ ለተባለው በማዕከል የሚገኘው ግዥ የገበያ ጥናት ባሙያው የፈፀመበት ሰነድ በማእከል ስለሚገኝ ሰነዱ ባለመያያዙ እንጂ መኖሩን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.5.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ግኝቱ ለላብራቶሪ ዕቃዎች፣ ለማገዶ እንጨት (አሁን ከኦዲት ሪፖርቱ የወጣ) እና ለሲቢሲ ማሽን ግዢዎች ቀርቦ የነበረ ሲሆን ከምላሹ ጋር የቀረበው የገበያ ዋጋ ጥናት ለማገዶ እንጨት ግዥ ብቻ በመሆኑ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

3.6 ከገደብ በላይ የተፈጸመ እና በቂ ተወዳዳሪዎች ያልተሳተፉበት የውስን ጨረታ ግዢ፣

3.6.1 ከገደብ በላይ የተፈጸመ የውስን ጨረታ ግዥ፣

3.6.1.1 ግኝት፣

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀፅ 1-3 በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች በሚለው ስር የመንግስት መ/ቤቶች በውስን ጨረታ ግዢ መፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት

ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው የሚል ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የግዢው መጠን ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

በተጨማሪም ከታህሳስ 1/2008 ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን እንደገና ለማሻሻል በወጣው መመሪያ ተራ ቁጥር 7 ላይ በውስን ጨረታ የሚገዛው ዕቃ ዋጋ ከብር 1,500,000.00 መብለጥ እንደሌለበት ተጠቅሷል፡፡

ይሁን እንጂ ለተማሪዎች ምርቃት የሚውል ጋወን፤ ኮፊያ እና ሪቫን ግዢ በሚል በመመሪያው ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን /Threshold/ በላይ ብር 1,554,570.00 (በመመሪያው ከታዘዘው በላይ ብር 54,570.00 ተጨምሮበት) በ28/10/2009 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 07137754 ወጪ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

3.6.1.2 <u>ስጋት፣</u>

ከውስን ጨረታ በመመሪያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን /Threshold/ በላይ የሆነ ግዢ መፈፀም መንግስት በውድድር ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

3.6.1.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ግዢዎች በአዋጁ፣ በደንቡ እና በመመሪያው መሠረት እንዲከናወኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

3.6.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ ዩኒቨርስቲው ለመጀመሪያ ጊዜ ባስመርቃቸው ተማሪዎች ገዋን በዩኒቨርስቲው አርማ እንዲሰራ የተደረገ በመሆኑ በአጋጣሚ የተመረቁ ተማሪዎች ቁጥር እየተገዛ ካለው ገዋን ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ሌላ አማራጭ በመጥፋቱ የተከሰተ ችግር መሆኑን በምላሹ ገልጿል፡፡

3.6.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ምርቃት በዕቅድ የሚከናወንና አስቀድሞ የሚታወቅ በመሆኑ ድንገተኛ ሊሆን ስለማይችል፣ ለምርቃት የሚሆን ጋወንም በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅቶ መቀመጥ ያለበት በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ለወደፊቱ በመመሪያው መሠረት መሠራት አለበት፡፡

3.6.2 በቂ ተወዳዳሪዎች ያልተሳተፉበት የውስን ጨረታ ግዢ፣

3.6.2.1 ግኝት፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 49 ውስን ጨረታ አፈፃፀም በሚለው ስር ንዑስ አንቀፅ 2 /ለ/ ላይ ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ውጤታማ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ እስከተቻለ ድረስ የተወዳዳሪዎቹ ቁጥር ከ5 /አምስት/ ማነስ እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲው በ2009 ዓ.ም ምረቃ በዓል የሚውል የድንኳን አገልግሎት ኪራይ እና ዲኮሬሽን አገልግሎት ለማሰራት በውስን ጨረታ 3 ዕጩ ተወዳደሪዎችን ብቻ በማወዳደር በ30/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0713449 ብር 378,801.15 ወጪ ተደርጎ ተገኝቷል።

3.6.2.2 ስጋት፣

አዋጁ ከሚያዘው መመሪያ ውጪ ጥቂት ተወዳዳሪዎችን ማሳተፍ የግዥውን ተዓማኒነት /ትክክለኛነት/ ማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑም በላይ መንግስት በውድድር ማግኘት የሚገባውን ጥቅም የሚያሳጣ ነው።

3.6.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና መመሪያ ከሚያዘው ውጪ አላግባብ የዕቃና የአገልግሎት ግዢ መፈፀም አግባብነት የሌለው መሆኑ ታውቆ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ግዢዎች በሚከናወኑበት ወቅት መመሪያ፣ ደንብ እና አዋጁን ተከትሎ እንዲከናወኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል።

3.6.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የሥራ አመራሩ ይህ ሊሆን የቻለው፣

- በቂ ተወዳዳሪ ሊገኝ ባለመቻሉ፣
- ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት ድንኳን በጣም ትናንሽና ለሚፈልጉት አገልግሎት ሊሆን ባለመቻሉ፣
- ውስን ጨረታው ውድቅ ቢደረግ ዩኒቨርስቲው አዳራሽ የሌለው በመሆኑ የአካባቢው አየር ፀባይ ደጋ በመሆኑና ዝናብ ቢዘንብ ዝግጅቱን ሊያበላሽ ስለሚችል፤ በከተማው ሰፊ አዳራሽ ባለመኖሩ፤ ዩኒቨርስቲው አዳራሽ የሌለው ስለሆነ ለምርቃ ስነ-ስርዓቱ የመጡ ወላጆችም በዚሁ ምክንያት እንዳይጉላሉ ግምት ተወስዶ የቀረቡት 3 ድርጅቶች ብቻ እንዲወዳደሩ መደረጉን ግንዛቤ እንዲወሰድ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል።

3.6.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ችግሩ በምላሹ የተጠቀሰው ከሆነ የምርቃቱ ጊዜም ሆነ ወቅቱ አስቀድሞ የሚታወቅ በመሆኑ አስቀድሞ የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ ግዥውን ቀጥታ ግዥን ጨምሮ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች መፈጸም ይቻል ነበር።

3.7 <u>የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ወጪ፣</u>

3.7.1 <u>ግኝት፣</u>

የገቢና የወጪ ሂሳቦች የተያዙትና የተመዘገቡት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 1,227,398.00 የትርፍ ሰዓት /Overload/ ክፍያ በሂሳብ መደብ 6116 (ለቋሚ ሰራተኞች አበል በሚለው) መመዝገብ እና ሪፖርት መደረግ ሲገባ በሂሳብ መደብ 6251 (በውል የሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎቶች) ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ ሲሆን በበጀት አርእስት 6116 ከላይ የተገለጸው የገንዘብ መጠን ሳይካተት ከበጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑን በበጀት ማነጻጸሪያ ላይ ለማረጋገጥ ተችሏል።

3.7.2 <u>ስጋት፣</u>

- የበጀት እጥረት ሲያጋጥም በመመሪያው መሰረት ከማዘዋወር ይልቅ ያልተሰራበት በጀት ካለው አርእስት በስህተት መዝግቦ የበጀት ሚዛኑ እንዲዛባ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የሂሳብ ገጽታ እንዳያመለክቱ እና የበጀት ዓመቱ የበጀት አጠቃቀም እንዲዛባ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.7.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ መያዛቸውን በማረጋገጥና በመከታተል በትክክለኛው የሂሳብ መደብ እንዲመዘገቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

3.7.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ የአመዘጋገብ ስህተት መሆኑን ጠቅሰው ወደፊት እንደሚስተካከል በምላሻቸው ገልጸዋል።

3.8 የህንፃ እና የመሰረተ ልማት ግንባታን በተመለከተ፣

3.8.1 ግኝት፣

ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ ለመዋላቸው እንዲሁም ሥራ ተቋራጮች በገቡት ውል መሠረት ለመፈጸማቸው ኦዲት ሲደረግ፣ ከዩኒቨርሲቲው ግንባታ ጽ/ቤት በተገኘ መረጃና ትንተና መሰረት፣ ከአፍሮ ፂዮን ኮንስትራክሽ ለተለያዩ የግንባታ ስራዎች በቀን 28/08/2008 (06/05/16) ተጀምረው በቀን 26/08/2010 (04/05/18) ይጠናቀቃል ተብለው በብር 881,787,388.10 ውለታ ከተገባባቸው ሥራዎች ውስጥ በብር 98,395,265.00 ውለታ የተገባበት የሳይት ወርክ ሥራ (የአዲሱ ዋናው ግቢ የአስፋልት ሥራ) እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታው ደረጃ (Project status) 14.73% ላይ የሚገኝ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

3.8.2 ስጋት፣

ለስራው የተሠጠው ጊዜ እየተጠናቀቀ ስለሆነ ተጨማሪ የጊዜ ማራዘሚያ እንዲጠየቅበት መንገድ የሚከፍት ሲሆን ይህ ደግሞ በተቋሙ የመማር ማስተማር እና በሌሎችም አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

3.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ሥራው በጊዜ ማራዘሚያ ሳይገፋ፣ በውል በተመለከተው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና የማስረከቢያ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቅና የተፈለገውን አገልግሎት ሊሰጥ እንዲችል ጥብቅ ክትትል ሊደረግበት ይገባል።

3.8.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፣

የሥራ አመራሩ በግኝቱ እና በማሻሽያ ሀሳቡ ላይ ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን፣ የሚመለከተው የሥራ ክፍል፣ ለዩኒቨርሲቲው ግንባታ ሥራ ለሁለት ታዋቂ ድርጅቶች የተሠጠና ድርጅቶቹም በጊዜ ገደቡ ለመጨረስ ጥረት በማድረግ ላይ ሲሆኑ አፈፃፀማቸውም ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ይህም 3 ድርጅቶች ማለትም (ሥራ ተቋራጭ፣ አማካሪ ድርጅትና ዩኒቨርሲቲው) ወርሃዊ የሥራ ግምገማ መድረክ ያላቸው ስለሆነ በጊዜ ገደቡ እንዲጨርሱ ስለሚያስገድዳቸው የተመደበው በጀት በቂ ካለመሆኑ የተነሳ የገንዘብ ዕጥረት ካልገጠመ በስተቀር ተጨማሪ የጊዜ ማራዘሚያ ሳይጠየቅ በውል ጊዜ ውስጥ ይፈፀማል የሚል እምነት እንዳላቸው፣ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ማስታወሻ በተሰጠው ምላሽ ገልጿል።

4. ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣

የዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳብ በፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4/ (ሀ - ሰ) ላይ በተዘረዘረው መሠረት መያዙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በሂሳብ መደብ 4253 ለአቅራቢዎች ከተሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ውስጥ፤ በ2009 በጀት ዓመት ለአንድ አቅራቢ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ብር 50,000.00 እስከበጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ መሆኑ፤ እና
- በሂሳብ መደብ 4274 በልዩ ልዩ ከተመዘገቡት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ውስጥ ብር 9,714.65 ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ ሂሳብ መሆኑ፤ ተረጋግጧል፡፡

4.2 ስጋት፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረድ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፤ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡን ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በተሰብሳቢነት የሚገኘው ገንዘብ ሳይወራረድ እንዳይቀር የሥራ አመራሩ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ፤ ለወደፊቱም ተቋሙ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የመንግሥት የፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ተከትሎ እንዲወራረድ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው በጥብቅ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- በሂሳብ መደብ 4253 የተያዘው ለመኪና ጥገና የወጣ ሲሆን ከምፓኒው በውጪ ምንዛሬ እጥረት መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ባለመገኘቱ በመሆኑን እና እነሱም እየተከታተሉ መሆኑን፣
- በሂሳብ መደብ 4274 የተያዘው ሠራተኛው ሥራ በመልቀቁ ምክንያት ሊሰበሰብ አለመቻሉን፣ ለዚህም ሰው ሀብት አስ/ዳይክቶሬት የሥራ መልቀቂያ እንዳይሰጥ መታዘዙን እና ጉዳዩ በሕግ እንዲጠየቅ ተደርጎ የህግ ዳይሬክተሩ ክስ የመሰረተ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

4.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በሂሳብ መደብ 4253 የተያዘው ከምፓኒው በውጪ ምንዛሬ እጥረት የመለዋወጫ ዕቃ ግዥ ባለመገኘቱ ለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበለት ቢሆን እንኳ ሂሳቡ ክትትል የሚያሻው ነው፡፡ በመሆኑም ሂሳቦቹ ክትትል ተደርጎባቸው ሊወራረዱ ይገባል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

5.1 <u>ግኝት፣</u>

የኮሌጁ ተከፋይ ሂሳብ በፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ (ሀ - ሠ) ላይ በተዘረዘረው መሠረት መያዙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሂሳብ መደብ 5002 በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች ተመዝግቦ ከሚገኘው ሂሳብ ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ ብር 374,245.31 እና ከሁለት አመት በላይ ብር 2,258,609.71፣ በድምሩ ብር 2,632,855.02 ውዝፍ ዕድሜ ያስቆጠረ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 5003 የጡረታ መዋጮ ተከፋይ ሂሳብ በሰኔ 30/2009 ሪፖርት ላይ ብር 8,890.22 በተከፋይነት በውዝፍ የሚታይ መሆኑ እና፤

5.2 <u>ስጋት፣</u>

በተካፋይነት የተያዙ ሂሳቦች በወቅቱ ለተጠቃሚዎቹ አለመክፈል ገንዘቡ ከዕቅድ ውጪ ለሆኑ ስራዎች እንዲውል መንገድ ይከፍታል።

5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ውዝፍ ዕድሜ ባስቆጠሩ ተከፋይ ሂሳቦች ላይ በመመሪያው መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ እና የጡረታ መዋጮ ሂሳብ ከሚመለከተው አካል ጋር በመናበብ ሂሳቡ የሚስተካከልበት መንገድ እንዲፈለግ፤ ለወደፊቱም የሥራ አመራሩ በተከፋይ ሂሳብ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

5.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ፣

- ሂሳብ መደብ 5003 ጡረታ መዋጮ የታየው ተከፋይ በሀምሌና ነሀሴ ወር ላይ ለሚመለከተው የተላከ መሆኑን፣ እና
- በሂሳብ መደብ 5002 የተያዘውን በተመለከተ ምላሽ ያልሰጡ ሲሆን የሚመለከተው የሥራ ክፍል የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ግብርና ኮሌጅ ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ ተነጥሎ ወደ አርሲ ዩኒቨርሲቲ ሲጠቃለል ቁርጥ ያለ ሂሳብ ባለመኖሩ ገንዘብ ወደ ገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ፈሰስ መደረጉን፣ ሂሳቡን ለማስተካከል በሂደት ላይ መሆኑን፣ ይህንንም ወደፊት በሪፖርት እንደሚገልጹ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ማስታወሻ በሰጠው ምላሽ ገልጿል።

5.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

- በሂሳብ መደብ 5003 የተያዘው የጡረታ መዋጮ በሀምሌነና ነሀሴ ወር ላይ ለሚመለከተው የተላከ ለመሆኑ ከምላሽ ጋር መስረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም በግኝቱ ላይ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

6. በጀት፣

6.1 ግኝት፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 24 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በሚለው ስር የተፈቀደ በጀት መኖሩ ሳይረጋገጥ ከተፈቀደለት በጀት በላይ ወጪ ማድረግ ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል የተመለከተ ቢሆንም፣ ለዩኒቨርሲቲው በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደለት የተስተካከለ በጀትና በስራ ላይ የዋለው ሂሳብ በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከመደበኛ በጀት ከ10% በላይ ያልተሰራበት በጀት ብር 3,207,627.81 እና ለየሂሳብ መደቦቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ብር 8,892,518.40 ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 4 ተመልክቷል)

6.2 ስጋት፣

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከፍተኛ ተራፊ በጀት መገኘት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሊሰሩ በዕቅድ የተያዙ ስራዎች ለመከናወናቸው አጠራጣሪ የሚያደርገው ሲሆን፤ በተጨማሪም በሌሎች መ/ቤቶች /ተቋማት/ ሊሰራበት የሚችለው በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ አሰራር ነው፡፡
- የበጀት ዝውውር ሣይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም መመሪያን ከመጣሱም ባሻገር የመንግሥትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጠጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡
- በጀት ሳይፈቀድ፣ ተጨማሪ በጀት ሳይጠየቅ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ወጪ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ አሰራሩ እንዲስተካከል መደረግ አለበት፡፡
- በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ ከበጀት በላይና በታች አፈፃፀም በበጀት ኮንትሮል (ቁጥጥር) ሙያተኛ እጥረት መሆኑን ጠቅሰው ትምህርት እንደተወሰደበት እና ወደፊት እንደማይከሰት በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

7. <u>ንብረት፣</u>

7.1 <u>የቋሚና አላቂ ንብረት አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፣</u>

7.1.1 <u>ግኝት፣</u>

□ፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪ□ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሁለት የቋሚ ንብረት አስተዳደር በሚለው ሥር አንቀጽ 7 የቋሚ ንብረት አመዘጋገብ ንኡስ አንቀጽ 1መ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር መስጠት ያለባቸው ሲሆን፣ ይህ ቁጥር በቋሚ ንብረቱ ላይ መለጠፍ ወይም መጻፍ እንዳለበት እና በተመሳሳይ መልኩ በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 አንቀፅ 5 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ሃላፊነት በሚለው ስር የመንግስት መስሪያ ቤቶች □በላ□ ኃላፊዎች የመ/ቤታቸውን ተልዕኮ ለማሳካት ስራዎች በአግባቡ እን□ከናወኑ ባሉት ህጎች ላ□ በመመርኮ□ □□በቀ ኢኮኖሚ□ዊ፤ ብቁና፤ □ሁ□ጋታማ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የመዘርጋት ሃላፊነት እንዳለባቸው በመመሪያው የተጠቀሰ ቢሆንም፣

<u>የቋሚ ንብረት፤</u>

- በዋናው ካምፓስ የአዲስና የተመላሽ የቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት ሠራተኛ ንብረት የመረከብ እና የገቢና ወጪ ደረሰኞች (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀት ሥራዎችን የሚያከናውኑ፣ በተጨማሪም የገቢና የወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ የሌለ መሆኑ፤
- ከሱቢ የጽህፈት መሳሪያና የቢሮ ዕቃዎች አቅራቢ ጋር የብር 811,998.00 ዋጋ ያላቸው 5 የተለያዩ ፈርኒቸሮች እንዲቀርብ በ22/05/2009 በተገባው ውለታ መሠረት፣
  - አቅራቢው ከ22/05/09-15/08/09 ባለው ጊዜ ውስጥ ንብረቶቹን አጠናቆ እንደሚያስረክብ፤
  - ከድርጅቱ ጋር የተገባው ውለታ ተቀባይ በመጠን፤ በዓይነትና በጥራት ለማቅረብ በሌላ በኩል ውል ሰጪም የአቅርቦቱ ዓይነትና ጥራቱን የጠበቀ ለመሆኑ በራሱ ኮሚቴና አቅራቢው በተገኘበት ወይም ራሱ ህጋዊ ውክልና በሰጠው ሰው አማካይነት ተቆጣጥሮ በአንጼ ተረክቦና ጭኖ እንደሚያጓጓዝ፣

- ውል ተቀባይ በጨረታ ያሸነፈባቸው ዕቃዎች በውሉ መሠረት በትክክል በአሃዝ በሰጠው ዋጋ መሠረት ብቻ ለውል ሰጪው ለአርሲ ዩኒቨርስቲ በሚፈልገው ዓይነትና መጠን በመጋዝኑ አዘጋጅቶ መጠበቅ እንዳለበት፤ በውሉ የተመለከተ ቢሆንም፣
    - ውለታ ከተገባባቸው 5 ዓይነት ቢሮ ዕቃዎች ሃይባክ ማኔጀሪያል ተሽርካሪ ወንበሮች ብዛት 80 እና የሴክሬታሪ ተሽከርካሪ ወንበሮች ብዛት 80፣ በድምሩ የብር 255,999.20 ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች አቅርቦ በጥራት ጉድለት ምክንያት ዕቃዎቹ ተመላሽ የተደረጉ ከመሆኑም በተጨማሪ ብር 159,999.96 ዋጋ ካላቸው ብዛት 80 የቢሮ ጠረጴዛዎች ውስጥ 35 (43.75%) የሚሆኑት ጭራሽ ማይገጠሙ ብረቶቻቸው በዋናው ግቢ ውስጥ ጸሃይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ያሉትን ጨምሮ የጥራት አረጋጋጭም በውለታው መሠረት የቀረቡ መሆኑን ባረጋገጠው መሰረት ሥራቸው ሳይጠናቀቅ (ሳይገጠሙ) በ23/09/09 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 824102 ተዘጋጅቶላቸው በውለታው መሰረት ላልቀረቡ ወንበሮች ለአቅራቢው አላግባብ ብር 69,999.65 (35*1999.99) የተከፈለ መሆኑ፤ (በንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 824102 ገቢ ከተደረገው የብር 347,999.66 ዕቃዎች ውስጥ)፣

- በዋናው ካምፓስ የአዲስና የተመላሽ የቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት ሠራተኛው ከቀድሞ የግምጃ ቤት ሠራተኛ ምንም ዓይነት ርክክብ ያልተፈጸመባቸው በአቅራቢዎች ለናሙና የቀረቡ የተለያዩ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፤(ለምሳሌ፤ ብርድልብስ፤ ሸሚዞች፤ የዝናብ ልብሶች፤ ስፖንጅ ፍራሾች)
- በዋናው ካምፓስና በግብርና ኮሌጅ ግቢ በ3 የቆርቆሮ ግምጃ ቤቶች እጅግ በጣም ብዛት ያላቸው ያልተጠገኑና ተጠግናው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የተማሪዎች የብረት አልጋ ያለምንም እርምጃ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በዋናው ካምፓስና በግብርና ኮሌጅ በቆርቆሮ ግምጃ ቤቶች በርካታ አሮጌ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፤ ክሊነሮች፤ ፕሮጀክተሮች (LCD)፤ የተለያዩ የላብራቶር ዕቃዎች፤ ያመሃ ሞተር ብስክሌት የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 4-0784 ኦሮ ለዓመታት በአሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት የተቀመጠ፤ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች፤ የተለያዩ የኤሌክሮኒክስ ዕቃዎችና ሌሎች የተለያዩ ንብረቶች በየግምጃ ቤቶቹ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- በዋናው ካምፓስ በኑሩ ሀሚድ የህንጻ መሳሪያ መደብር የቀረቡና በጥራት ችግር ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ያልተረከባቸው የተባሉ ሞራሌ ያለምንም እርምጃ በግቢ ውስጥ ጸሃይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው መሆኑ፤
- በግብርና ኮሌጅ የቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት የተማሪዎች ዶርም በገነባው ጭላሎ ኮንስትራክሽን ከ2 ዓመት በፊት በአደራ የተቀመጡ 12 አነስተኛ እሳት አደጋ መከላከዎች፤ እንዲሁም 4 ትልልቅ የእሳት አደጋ መከላከያዎች ደግሞ በንብረትነት የተመዘገቡ በዩኒቨርስቲው የግንባታ ጽ/ቤት ሃላፊ የቃል ትዕዛዝ የተቀመጡ በህንጻዎቹ ላይ መተከል (መገጠም) ሲገባው ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- በICT የሥራ ክፍል ጠያቂነት ተገዛ የተባለ ኬብል ትራክ ብዛት 600 ብር 30,000.00 ዋጋ ያለው ያለአገልግሎት ከ1ዓመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፤

<u>የተማሪዎች ክሊኒክ መድሃኒትና የህክምና አገልግሎት፤</u>

- በግብርና ኮሌጅ፣
  - ከዚህ ቀደም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ መድሃኒቶች የተወገዱ ቢሆንም አሁንም ዓይነታቸውና ብዛታቸው በዝርዝር ያልተለዩ በመድኃኒት ግምጃ ቤትና በመድኃኒት ማደያ ክፍል (Dispencery Room) የሚገኙ መሆኑ፣
  - በኮሌጁ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በመድሃኒት ግምጃ ቤት የሚገኙት መድኃቶች ቆጠራ ሲደረግ በመድኃኒት ማደያ የሚገኙት ቆጠራ ያልተቆጠሩ መሆኑ፣
  - ኮሌጁ መድኃኒትና የህምና ዕቃዎች በቀጥታ ከአሰላ ሪፈራል ሆስፒታል እየጠየቀ በማምጣት በመጠቀም ለሆስፒታሉ ክፍያው እንደሚፈጸም ቢገለጽም ክሊኒኩ በየጊዜው መድሃኒት ሲጠይቅ አስቀድሞ ተጠይቆ ከመጣው በመድኃኒት ግምጃ ቤትና በመድኃኒት ማደያ ያለው ቀሪ ሳይታወቅ ሌላ እየተጠየቀ የሚመጣ መሆኑ፤

<u>የጽህፈትና ሌሎች አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት፤</u>

- በዋናው ካምፓስ የአላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት በኮኪ ሥራ አቅራቢ ድርጅት የቀረቡ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ የተደረገባቸው፤ በካርቶን ቦክስ ፋል 10፤መዝገብ ትልቅ 16፤ ከለር ወረቀት 10፤ ፕሮቶኮል መዝገብ 7፤ የፕሪንተር ወረቀት 4፤ ፖስታ የተለያየ መጠን ያላቸው 30፤ ሰስፔንሽን ፋይል 30፤ ለዕቃ ርክክብ ያልተፈጸመባቸውና በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ገና ያልታዩ አቅራቢው ካቀረባቸው ከ8 ቀናት በላይ የሆናቸው ንብረቶች ለዕቃ ግምጃ ቤትነት ባልተዘጋጀ ክፍል ውስጥ ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው በወለል ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤

- በዋናው ካምፓስ ተገዛው መጠን ወዲያውኑ ወጪ የሚደረጉ አላቂ እቃዎች ገቢ እና ወጪያቸው በቢን ካርድና በስቶክ ካርድ ላይ የማይመዘገቡ መሆኑ፤
- ዩኒቨርስቲው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤ የንብረት የገቢና ወጪ (ሞ/19 እና ሞ/22) እንዲሁም የተለያዩ የሂሳብ የወጪ ሰነዶችን ኮሌጆች ከዋናው ካምፓስ እንዲወስዱ ሲደረግ (መውሰድ ሲጀምሩ) አስቀድሞ ኮሌጆቹ በአዳማ ዩኒቨርስቲ ሥር በነበሩበት ወቅት የወሰዱአቸው፣ በተለይ ያልተሰራባቸው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤ የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች እንዲሁም የተለያዩ የሂሳብ የወጪ ሰነዶች ርክክብ ሳይፈጸም በሠራተኞቹ እጅ የሚገኙ መሆኑ፤

<u>**የተማሪዎች ምግብ ግብዓቶችና ሌሎች ዕቃዎች፤**</u>

- በየዕለቱ ከአቅራቢው (ሣጉሬ ዳቦ ቤት) ለዋነው ግቢ የሚቀርበው ዳቦ የግምጃ ቤት ሠራተኛዋ ያለምንም ታዛቢና የጥራት አረጋጋጭ በቀጥታ ከአቅራቢው የሚረከቡ ከመሆኑም በተጨማሪ የሚቀርበው ዳቦ በውለታው መሰረት መጠኑን (ግራሙን) ጠብቆ እየቀረበ መሆኑን በናሙና እንኳ እየተመዘነ የማይረጋገጥ መሆኑ፤
- ከጤፍ አቅራቢዋ (ሙሁዋባ) ከውለታ በፊት (ውለታ ሳይገባ) 2 ቀን (በ5/08/09 እና 7/08/09) ከቀረቡትና በጥራት አረጋጋጭም ተረጋግጦ ካለፈው 138.58 (64.94+73.64) ኩንታል ጤፍ ውሰጥ፣
    - 105 ኩንታሉ ጥራቱን ያልጠበቀ (ቀጭ ቀጭ ያለው) መሆኑ እየታወቀ ከሌላ ጤፍ ጋር በ20/09/2009 የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ቁጥር 494756 ተዘጋጅቶለት አላግባብ ብር 249,795.00 (105*2379) ለአቅራቢዋ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ (በንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 494756 ገቢ ከተደረገው ብር 593,275.02 ውስጥ)
    - ከላይ ከተጠቀሰው ጥራቱን ያልጠበቀ 105 ኩንታል ጤፍ ውስጥ 75 ኩንታሉ በጤፍ ግምጃ ቤት፣ 30 ኩንታሉ ደግሞ በሚኒስቶር ያለምንም እርምጃ የተቀመጠ ከመሆኑም በተጨማሪ በተበላሸው ጤፍ ላይ እርምጃ ሳይወሰድ አቅራቢዋ አሁንም ጤፍ እያቀረቡ መሆኑ፤
    - ከአቅራቢዋ ጋር በ20/08/09 የተገባው ውለታ ከ29/12/08-28/12/09 (ለ1ዓመት) እንደገባ ተደርጎ ካቋረጠው አቅራቢ የተገባውን የውለታ ጊዜ በመጠቀም ውለታ የተገባ መሆኑ፤ (ቀጭ ቀጭ ጤፉ አስቀድሞ በነበረው አቅራቢ እንደቀረበ አሊያም አቅራቢዋ አስቀድሞም ታቀርብ እንደነበረ ለማድረግ የተደረገ መሆኑ)

- ለግብርና ኮሌጅ ተማሪዎች ቀለብ አስቀድሞ ጨፍ ለማቅረብ ከ29/12/08-28/12/09 (ለ1ዓመት) ውለታ የገባው ከበበ ለሜሣ የብዕርና የአገዳ ሰብሎች አቅራቢ ውለታውን ሲያቋርጥ በዩኒቨርሲቲው ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- በምግብ ዕቃዎች ሚኒ ስቶር ወስጥ በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የተቀመጡ (የማይሰሩ) 2 ፍሪጆች፤ በኩዊታል በውጭ የተከመረ ብዛት ያለው የጤፍ ብጣሪ ያለምንም እርምጃ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በግልጽ ጨረታ ተወዳድረው በአሸናፊነት የተመረጡ የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃና ማጣፈጫዎች አቅራቢዎች የሚያቀርቡአቸው ዕቃዎች የጥራት ማነስ (ጉድለት) በሚታይባቸው አቅራቢዎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ በዕቃው ተጠቃሚ ክፍሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የበላይ ሃላፊዎች በጽሁፍ ሪፖርት የሚደረግ ቢሆንም ሪፖርት የተደረገለት አካል ሁኔታውን አጣርቶ እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፤ (ለናሙና፤ ከተማሪዎች ጉዳይ ቡድን መሪ በ01/10/09 በተጻፈ ደብዳቤ ድንች፤ጥቅል ጎመን፤ የምግብ ጨው፤ ቃሪያና ቀይ ሽንኩርት አቅራቢዎች የሚያቀርቡት ዕቃ ጥራቱን ያልጠበቀ መሆኑ ተማሪዎች ጉዳይ ተ/ዲን ሪፖርት የተደረገ)፣ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

7.1.2 ስጋት፣

- የንብረት ገቢና ወጪ መከታተያ አለመኖር የንብረት ከወጪ ቀሪን በቀላሉ ለማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑም በተጨማሪ ንብረቱ ቢጠፋ ወይም ቢጎድል ወዲያውኑ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡
- የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞች ያልተረከቡትን ንብረት በዕቃ ግምጃ እንዲያስቀምጡ ማድረግ ንብረቱ ቢጠፋ (ቢጎድል) ሠራተኛውን ተጠያቂ ለማድረግ የማያስችል አሰራር ከመሆኑም በተጨማሪ አለመግባባት እንኳ ቢከሰት መፍትሄ ለመስጠት አያስችልም፡፡
- በውለታው መሰረት ተጠናቀው ያልቀረቡ ንብረቶችን ተረክቦ ገቢ ማድረግና ጥራቱን ያልጠበቀ መሆኑ አስቀድሞ የታወቀ ጤፍ ገቢ በማድረግ ክፍያ መፈጸም የመንግስት ገንዘብ ለግለሰቦች መጠቀሚያነት እንዲውል መንገድ የሚከፍት አሰራር ነው፡፡
- ለናሙና የሚቀርቡ ንብረቶች ያለምንም ርክክብ በግምጃ ቤት እንዲጠበቁ ማድረግና ሠራተኞችም ሲቀያየሩ ንብረቶቹ በጽሁፍ (በመረካከቢያ ቅጽ) ለተከታዩ

አለማስተላለፍ በንብረቶቹ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ተጠያቂውን ለመለየት አያስችልም፡፡

- ኮሌጆች አስቀድሞ የወሰዱአቸው ያልተሰራባቸው የገንዘብ መሰብሰቢያ እና የንብረት ደረሰኞችን የተሰራባቸውና ያልተሰራባቸው በአግባቡ ተለይተው ርክክብ አለመፈጸም በተላይ በገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞቹ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ገንዘብ እንዲሰበሰብባቸው መንገድ የሚከፍትና ለክትትልና ለቁጥጥር አመቺ አይደለም፡፡
- ለእሳት አደጋ መከላከያነት የቀረቡ ንብረቶች በንብረትነት ሳይመዘገቡና ለታለመላቸው ዓላማ ሳይውሉ ለዓመታት ያለአገልግሎት ማስቀመጥ አደጋ ቢከሰት ለመከላከል አያስችልም፡፡
- በቋሚ ንብረቶች አካል ላይ መለያ ቁጥር አለመኖር ለክትትልና ለቁጥጥር አመቺ አይደለም፡፡
- በአሮጌ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ ንብረቶቹ ለበለጠ ብልሽት እንዲዳረጉና አግባብ ያልሆነ የጥገና ወጪ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በአቅራቢዎች በሚቀርቡ ዕቃዎች ላይ በዕቃው ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች በሚያቀርቡት የዕቃዎቹ የጥራት ጉድለት ሪፖረት አጣርቶ እርምጃ አለመውሰድ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ለግለሰቦች መጠቀሚያነት እንዲውል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ለተጨማሪ ወጪ ይጋብዛል፡፡

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለመቅረፍ የንብረት አስተዳደር፤ አጠቃቀምና አያያዝ ስርዓቱን ማስተካከል ይኖርበታል፡፡ አሠራር ባበላሹና ዩኒቨርሲቲው ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያጣ ባደረጉት ላይም ጉዳዩ በተጨማሪነት ተጣርቶ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

7.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የሚመለከተው የሥራ ክፍል፡-

- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉት ኮሌጆች ራሳቸውን ችለው እንዲተዳደሩ በማድረግ ሂደት ላይ ስለሆነ አሁን ባለው ሁኔታ ሠራተኞች ቁጥር ከተማሪ ቁጥር ጋር እየተጠጋጋ ስለሆነ ቅጥር ላለመፈፀም መታገስ ስለተመረጠ መሆኑን፣ ወደፊት ግዥዎች የሚፈፅሙት በኮሌጁ ደረጃ እንደሚሆን፣ የስቶክ መቆጣጠሪያ እንዲሠራ ሠራተኛውን በማብቃት ላይ እንደሚገኙ፣

- ከሱቢ የጽህፈት መ/እና የቢሮ እቃዎች አቅራቢ ድርጅት ከውሉ ጊዜ ውጪ ለመረከብ የተገደዱት ሌላ ጨረታ ቢወጣ ተጨማሪ ወጪና ጊዜ ስለሚጠይቅ ሊታገሱ መቻላቸውን፣ ሳይገጠሙ ርክክብ የተደረገባቸው የሠራተኞቻቸው ስህተት ስለሆነ እርምጃ ተወስዶባቸው እንዲገጠሙ በመደረግ ለይ መሆኑን፣
- የቀድሞ ሠራተኛና የአዲሱ ሠራተኛ ርክክብ ሂደት የዘገየው ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የተጓጓዙ ንብረቶች ከአጓጓዘው ሠራተኛ ተመዝግቦ ርክክብ ባለመጠናቀቁ ስለሆነ ይህን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚያጠናቅቁ፣
- ተከማችተው የሚገኙት የብረት አልጋዎች ተጠግነው ቢወጡ ማስቀመጫ ቦታ ስለሌለ እንግልትና መሰባበር ስለሚፈጠርባቸው ተጨማሪ ዶርሞች ሲገነቡ ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ታሳቢ በማድረግ መሆኑን፣
- በርካታ አሮጌና የተጎዱ ኮምፒተሮችንና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች በመወገድ ሂደት ላይ መሆናቸውን፣ እና
- በኑሩ ሀሚድ ህንፃ መሳሪያ መደብር ቀርበው በጥራት ጉድለት ያልገባ ሞራሌዎች እንዲወገድ በማድረግ ሂደት ላይ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ማስታወሻ በተሰጠ ምላሽ የገለጸ ሲሆን፣

በሥራ አመራሩ ምላሽ ደግሞ፣

- የተማሪዎች ዳቦ ጥራትና መጠን በተቆጣጣሪ ኮሚቴ (የተማሪዎች ተወካዮች የሚሳተፉበት) እየተጣራ እንደሚገባ፣
- 105 ኩንታል ጤፍ ቀጭቀጭ ያለው ጤፍም በኮሚቴው ተመርምሮ ከገባ በኃላ ቀጭቀጩ ሊታወቅ የቻለው የተወሰነው ያህል ተፈጭቶ ከተጋገረ በኃላ መሆኑን፣ ነገር ግን እንደታወቀ አቅራቢው ተለዋጭና ጥራት ያለው (ቀጭቀጭ የሌለው) እንዲያቀርብ ተደርጎ ቀጭቀጭ የነበረውን መልሶ እንዲወስድ መደረጉ፣
- የጥራት ማነስ የሚታይባቸው የማጣፊጫ ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ላይ እርምጃ አለመውሰድ ለተባለው ግብዓቶቹ የጥራት ጉድለት ካለባቸው የጥራት ተቆጣጣሪ ኮሚቴ (የተማሪ ተወካይ ያለበት) እንደማያሳልፍ እና በጥራት ተቆጣጣሪዎች የቀረበ የጥራት ጉድለት ሪፖርት የሌለ መሆኑ፣

ተገልጿል፡፡

7.1.5 **የኦዲተሩ አስተያየት፣**

በተለይ በሥራ አመራሩ ለተሰጡ ምላሾች ማረጋገጫ ያልቀረበ በመሆኑ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

7.2 **የተሽከርካሪዎችን አያያዝን በተመለከተ፣**

7.2.1 **ግኝት፣**

በፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል አራት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ሰ) የመንግሥት መ/ቤት በግዥ፣ በስጦታ፣ በዝውውር…ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ፤ የተሽከርካሪውን አይነትና ሞዴል፣ የጭነቱ ልክ (በሰው፣ በኩንታል፣ በኪዩቢክ ሜትር ወይም በሊትር ተለይቶ)፤ የቻንሲና የሞተር ቁጥሮች፣ የሚጠቀመው የነዳጅ አይነት፤ የተገዛበት ወይም በመ/ቤቱ ባለቤትነት ሥር የዋለበት ቀንና ዓመተ ምህረት፤ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር መዝግቦ መያዝ እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲው ካሉት 66 ተሽከርካሪዎች ውስጥ፤

- 18 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፤
- የ8 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ መቆጠሪያ (ጌጅ) የማይሰራ መሆኑ፤
- 48 ተሽከርካሪዎች ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት /ኖርማላይዜሽን/ ያልተሰራላቸው /የሌላቸው/ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 7 ተመልክቷል፡፡)

7.2.2 ***ሥጋት፣***

- የሊብሬዎች አለመኖር የተሽከርከሪዎቹን ባለቤትነት ጥያቄ ውስጥ ሊከት ይችላል፡፡
- የነዳጅ ጌጅ አለመሥራት እና የኖርመላይዘሽን አለመሠራት በነዳጅ አጠቃቀም ላይ ብክነት ሊያስከትል ይችላል፡፡

7.2.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ ለሌላቸው ተሽከርካሪዎች ሊብሬው እንዲወጣ፤ የነዳጅ ጌጅ መቆጠሪያቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው እንዲጠገን ማድረግ እና ኖርማላይዜሽን /ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት/ ያልተሰራላቸው /የሌላቸው/ ተሽከርካሪዎች ኖርመላይዘሽኑ እንዲሠራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

7.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣

- 66 የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች ከተባሉት ውስጥ 5ቱ ትራክተሮች፣ 6ቱ ደግሞ ሞተር ሳይክሎች ሲሆኑ 6 ተሽከርካሪዎች በጥገና ላይ ያሉ፣ 5 ተሽከርካሪዎች ለረጅም ጊዜ የቆሙና ተጠግነው አገልግሎት ይሰጣሉ ተብለው የሚገመቱ መሆናቸውን፣ በአጠቃላይ 22 ተሽከርካሪዎች በተለያየ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን 44 በማዕከላዊ አስተዳደና በየኮሌጆቹ አገልግሎት እየሠጡ የሚገኙት ተሽከርካሪዎች መሆናቸውን፣
- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ከሌላቸው 18 ተሽከርካሪዎች ውስጥ ዩኒቨርሲቲው አዲስ እንደመሆኑ መጠን የዩኒቨርሲቲውን ተሽከርካሪ እጥረት ግምት ውስጥ በማስገባት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የተለያየ ሞዴልና የመጫን አቅም ያላቸው 12 ተሽከርካሪዎች በዲክሌራሲዮን ምክንያት ሊብሬ ሳይሰጣቸው የተሽከርካሪዎቹ ሰሌዳና ቦሎ ብቻ ተሰጥቷቸው ስለነበር እስካሁን የዲክሌራሲዮኑን ጉዳይ በመከታተል፡ ለማስፈፀም በሂደት ላይ እንደሚገኙ፣ የዲክሌራሲዮኑ ጉዳይ እንደተጠናቀቀ ሊብሬውን የሚረከቡ መሆኑን፣
- የነዳጅ ጌጅ መቆጣጠሪያ የማይሠራ 8 ተሽከርካሪዎች የተባሉት መረጃው ቀደም ሲል ከቀረበው የተወሰደ ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ በግብርና ኮሌጅ 2፣ በበቆጂ ካምፓስ 1፣ በድምሩ 3 ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሠራ ለኮሌጆቹ ያሣወቁ መሆኑን እና ይህም በመለዋወጫ እጦት ምክንያት የተከሰተ ሲሆን ወደፊት የሚሻሻል እንደሆነ፣

ኖርማላይዜሽን ያልተሠራላቸው ተሽከርካሪዎች አብዛኞቹ በብልሽት ምክንያት የቆሙና ጥገና እየተደረገላቸው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች መሆናቸውን፣ አንዳንዶቹ በተደራቢ ሥራዎች ምክንያት ቢዘገዩም በሥራ ላይ ያሉ ኖርማላይዜሽን ያልተሠራላቸው ተሽከርካሪዎች በሙሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሠራላቸው የሚደረግ መሆኑን፣በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

8. ልዩ ልዩ፣

8.1 ዩኒቨርሲቲው ለመኖሪያነት የተከራያቸው ቤቶችን በተመለከተ፣

8.1.1 ግኝት፣

ዩኒቨርሲቲ ለመምህራን መኖሪያነት ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ በማድረግ ከግለሰቦች ለተከራያቸው ቤቶች የተከፈለው ሂሳብ ትክክለኛነትና ቤቶቹ ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

- ቤት ለመከራየት የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ08/05/09 ከዩኒቨርሲቲው በተጻፈ ደብዳቤ ተጠይቆ ከኤጀንሲው በ9/06/09 በቁጥር መግኤ/አ-51/2/1668 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም የቤቶቹ የኪራይ ሂደት ከኤጀንሲው ተጠይቆ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ዩኒቨርሲቲው የመኖሪያ ቤቶችን ለመከራየት ህዳር 12/2009 አሰላ በሚገኘው ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ ጣቢያ የጨረታ ማስታወቂያ በማስነገር በውድድር አሸናፊዎችን በመምረጥ የቤቶቹ የኪራይ ሂደት ኤጀንሲው ተጠይቆ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት የተጠናቀቀ መሆኑ፤ (ለምሳሌ፤ ከኤጀንሲው ስምምነት ከ09/06/09 በፊት ከ01/06/09 ጀምሮ ለ5 ወራት ከአቶ ረታ ብርሃነ ቲኦቲ ጨምሮ በብር 45,900.00 ሂሳብ የብር 229,500.00 /45,900.00 * 5/ ውለታ የተገባ መሆኑ፣ ለኪራይ የቀረቡት ቤቶች ለስፔሻሊስት ሃኪም መምህራን ምቹና ሳቢ መሆናቸው እንዲያረጋገጥ የተሰየመው ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ከማቅረቡ አስቀድሞ ውለታ የተገባ መሆኑ ማለትም ውለታ የተገባው በ1/06/09 ሲሆን የኮሚቴው ውሳኔ በ14/06/09 መሆኑ)
- የመኖሪያ ቤት ለመከራየት የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጄንሲ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ ላይ የሚከራዩ ህንጻዎችን የሚለይ ልዩ ኮሚቴ በማቋቋም መስፈርቱን የሚያሟሉ ከለየ በኂላ በካሬ ሜትር የሚያከራዩበትን ዋጋ በመጠየቅ በዋጋ ማቅረቢያ የግዢ ዘዴ ዝቅተኛ የካሬ ሜትር የኪራይ ዋጋ ከሰጠው ጋር ውለታ በመግባት ግዢውን መፈጸም እንደሚቻል የፈቀደ ቢሆንም ተወዳዳሪዎቹ የሚያከራዩበትን ዋጋም ሆነ የሚያከራዩትን ቤት ካሬ የሚያመለክት የጽሁፍ ማስረጃ ያለቀረቡ በመሆኑ በየተወዳዳሪዎቹ የተመለከተው የመወዳደሪያ ዋጋ የተገኘበት አሰራር የማይታወቅ መሆኑ፤
- ዩኒቨርስቲው ከ4 ግለሰቦች የተከራያቸው በቁጥር 12 ቤቶችን (1 ህንጻ 9 የተለያዩ ክፍሎች ወይም መኝታዎች የያዘና ሌሎች 3 ቤቶች) በተመለከተ የተጠየቀው ዝርዝር መረጃ ዘግይቶ በ27/10/09 የቀረበ እና ዝርዝር መረጃው 8ቱ (በህንጻው ካሉት 5ቱ እና ለየብቻ ያሉት 3ቱ) ለተጠቃሚዎች መተላለፋቸውን የሚያመለክት ቢሆንም ከዩኒቨርሲቲው የገቢያ ጥናት ባለሙያ ጋር በመሆን አስቀድሞ በ16/10/09 በተደረገ የመስክ ኦዲት ቅኝት ወቅት በህንጻው ከሚገኙ ቤቶች 6 ቱም ስቱዲዮዎች ለተጠቃሚዎች አለመተላለፋቸው የተረጋገጠ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ቤት ተከራይቶ ከሰጣቸው ተጠቃሚዎች ጋር ውለታ የሌለው መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው በፋሲሊቲ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሥር የመኖሪያ ቤቶችና ስታፍ ላውንጅ የሥራ ክፍል ያለው ቢሆንም የተጠቀሱት በኪራይ የተገኙ ቤቶች ወደ የሚመለከተው የሥራ ክፍል ባለመተላለፋቸው በማን ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው የማይታወቅ መሆኑ፤

- በዩኒቨርሲቲው ከአገልግሎት ሰጪዎች የሚፈጸሙ ውለታዎች ለአገልግሎት ሰጪዎቹ ለክርክርና መንግስትን አግባብ ላልሆነ ወጪ በሚዳርግ መልኩ የሚዘጋጁ መሆኑ፤ (ለምሳሌ፤ ከ4 ግለሰቦች የኪራይ ውለታዎች ለመምህራን መኖሪያ ቤት ኪራይ ከወ/ሮ ገነት ተሾመ ጋር በተደረገ ውል አንቀጽ 3 ላይ ከመጋቢት 1/09-ሰኔ 30/09 አራት ወራት መሆን ሲባው ለ5 ወራት የሚል ከመሆኑም በተጨማሪ በዚሁ ውለታ አንቀጽ 2 አስገዳጅ ስምምነቶች ሥር ደግሞ ከጥር 30/2009 - ጥር 30/2010 የሚያመለክት መሆኑ፤በተመሳሳይ ሁኔታ ከአቶ ደጀኔ ፈለቀ ጋር የተገባው ውል አንቀጽ 3 ከመጋቢት 1/09- ሰኔ 30/12/09 የሚጠናቀቅበት ሰኔ ብሎ ነሃሴ/09 ከማለቱም በተጨማሪ አንቀጽ 2 አስገዳጅ ስምምነቶች ሥር ከየካቲት 22/06/09 - የካቲት21/2010 የሚል መሆኑ) በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

8.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- ዩኒቨርሲቲው ከግለሰቦች ለተከራያቸው ቤቶች ከተጠቃሚዎቹ ጋር ውለታ አለመኖር ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የማያስችል ከመሆኑም በተጨማሪ በቤቶቹ አያያዝና አጠቃቀም ወቅት ጉድለት ቢከሰት እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡
- የቤቶቹን ምቹነት እንዲያረጋግጥ የተሰየው ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ሪፖርት ሳይቀርብ እንዲሁም ከግዢ ኤጀንሲ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ተወዳዳሪዎቹ ቤቶቹን የሚያከራዩበት ዋጋና ካሬ የሚያመለክት ማስረጃ (የዋጋ ማቅረቢያ) ሳያቀርቡ ማወዳደር የአገልግሎት ግዢውን ግልጽነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡
- የመኖሪያ ቤቶቹ አግባብ ላለው የሥራ ክፍል አለመተላለፍ በአንድ ወጥ መረጃ ለማግኘትና እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የማያስችል ከመሆኑም በተጨማሪ ያለአገልግሎት እንዲቆዩ ክፍተት ይፈጥራል፡፡
- አስቀድሞ የግዢ ሂደቱ ለተጠናቀቀ የአገልግሎት ግዢ የመንግሥት ግዥና አስተዳደር ኤጀንሲው የተጠየቀበት አግባብ አሠራሩ ግልጽት እንዲጎለው ያደርጋል፡፡
- በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር የሚያደርጋቸው የውል ስምምነቶች የዩኒቨርሲቲውን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ መዘጋጀታቸው ሳይረጋገጥ ውለታ መግባት ከአቅራቢዎች ጋር አለመግባባት እንዲፈጠር የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን አግባብ ላልሆነ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

8.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥ የግዢ ሥርዓትን /ደንብና መመሪያ/ በጠበቀ መልኩ እንዲፈፀም፤ በአያያዝና በአጠቃቀም ጉድለት በመንግስት ላይ ከፍተኛ የጥገና ወጪ /አግባብ ያልሆነ ወጪ/ እንዳያስከትሉ ከቤት ተጠቃሚዎች ጋር ውለታ እንዲኖር እና በሌሎቹም በቤቶቹ አያያዝና አጠባበቅ ላይ በሚታዩ በእያንዳንዱ ግድፈቶች ላይ የሥራ አመራሩ አፋጣኝ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

8.1.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- ከመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተደረገውን የቤት ኪራይ መጻጻፍ በተመለከተ ከነበረው ከፍተኛ የሆነ የስፔሻሊስት ሐኪሞች የመኖሪያ ቤት ጥያቄና ይህም በቶሎ ምላሽ ባለመሰጠቱ ምክንያት ስፔሻሊስት ሐኪሞቹን መምህራን ዩኒቨርሲቲውን እየለቀቁ ስለነበር ከፌደራል ግዢ ኤጀንሲ መ/ቤት ደብዳቤ ዩኒቨርሲቲው ፅፎ በሀሳቡ መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ ደብዳቤ እስኪመጣ ድረስ የሐኪሞቹን ጥያቄ ባፋጣኝ መመለሱ አማራጭ የሌለው ስለነበር የተፈፀመ ኪራይ መሆኑን፡
- ስድስት ስቱዲዮዎችን በወቅቱ መምህራን ያልፈለጉ በመሆኑ ያልተላለፉ ሲሆን አሁን ግን የቤት ማጣት ችግር ከፍተኛ በመሆኑ ለጊዜው ቤቶቹን መምህራኖች መረከባቸውን፣
- ዩኒቨርሲቲው ቤት ተከራይቶ ከሰጣቸው መምህራን ጋር ውል መፈጸሙን፣
- የመኖሪያ ቤቶቹ አግባብ ላለው የሥራ ክፍል በመኖሪያ ቤቶችና ስታፍ ላውንጅ አስተባባሪ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ መደረጉን፣

በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

8.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የተሰጡ ምላሾች አጥጋቢ ሆነው አልተገኙም፣ በማስረጃም አልደገፉም፡፡ ስለሆነም በማሻሽያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

8.2 የመምህራንና ሠራተኞች መኖሪያ ቤቶችን በተመለከተ፣

8.2.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት የግዢ እና የንብረት አሰተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 64፤66 ቁጥር 1 እና 2 የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ማናቸውም የመንግስት ንብረት የመ/ቤቱን ሃላፊነት ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ አገልግሎት ላይ መዋሉን የማረጋገጥ፤ የመንግስት መ/ቤት የበላይ ሃላፊ ሚኒስትሩ (የገ/ኢ/ት/ብ/ሚ/ር) በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ የጥገና እና

የእክብካቤ ስርዓት መዘርጋት እንዲሚገባ፤ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የበላይ ሃላፊና ሠራተኞች የመንግስት ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ ሃላፊነት እንዳለባቸው አዋጁ ቢያመለክትም፤ የተቋሙ የመምህራንና ሠራተኞች መኖሪያ ቤቶች አያያዝ፤ አጠባበቅና እደላ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ዩኒቨርስቲው በተለያዩ ቦታዎች (ሳይቶች) በበቆጂ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ 31፤ በግብርና ኮሌጅ 121፤ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ 10፤ በዲንሾ 67 በጠቅላላው ካሉት 229 የተለያየ ደረጃ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ያሉት ሲሆን፤

- ከተጠቀሱት በተለያየ ሳይት ከሚገኙ የተለያየ ደረጃ ያላቸው ቤቶች ውስጥ በበቆጂ 27፤ በግብርና 10፤ በዲንሾ ኮንዶሚኒየም 23፣ በድምሩ 60 ቤቶች ለጠተቃሚዎች ያልተላለፉ መሆኑ፣
- ዲንሾ ሳይት ከሚገኙ 2 ክሎክ የኮንዶሚኒየም 67 የተለያየ ደረጃ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ውሰጥ፤
    - ለተጠቃሚዎች ያልተላለፉ ቤቶች 8 ባለ 1፤ 1 ባለ 3፤ 10 ስቱዲዮ፣ በጠቅላላው 19 ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ ካለመሆኑም በተጨማሪ ከተጠቀሱት ቤቶች ውሰጥ 4 ሰቱዲዮዎች ወደ 2 ለመለወጥ (ለማስፋት) መሃላቸው የፈረሰና ያልተሰሩ መሆኑ፣
- በግብርና ሳይት ከሚገኙ 121 የተለያዩ ቤቶች ውስጥ 10 ዶርሞች ለተጠቃሚዎች ያልተላለፉ መሆኑ፣
- በቆጂ ከሚገኙ ለተጠቃሚዎች ካልተላለፉት 27 ቤቶች ውስጥ 5ቱ በህጋዊነት የተሰጣቸው ለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበና ምንም ዓይነት ውለታ በሌላቸው የኮሌጁ ሠራተኞች የተያዙ ከመሆኑም በተጨማሪ በመኖሪያዎቹ ግቢ ውስጥ የዩኒቨርሲው አካል ያልሆነ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የመብራት ሃይል የኮንክሪት ፖል የሚያመርት ሲሆን ይህ በማን እንደተፈቀደ የማይታወቅ መሆኑ፣
- ዩኒቨርስቲው ከበቆጂ ከተማ አስተዳደር ያለ ማስረጃ በስጦታ የተረከባቸው የተለያየ ደረጃ ያላቸው 31 ቤቶች ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ ጥገና የተደረገላቸው ቢሆንም በአብዛኛው (27ቱ ወይም 88%) አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ከመሆኑም በተጨማሪ ጥገና የተደረገላቸው ከተባሉት ቤቶች ውስጥ ጭራሽ በር የሌላቸው የሚገኙ መሆኑ፤ (ለናሙና፤ በር ስለሌለው እንስሳት የሚያድሩበት 1 ስቱድዮ ቤት፤ ለ14ቱ ቤቶች የሚያገለግል ሻወር ቤትና ማጠቢያ ክፍል በር ስለሌለው የቆሻሻ አሮጌ ዕቃ ማከማቻ መሆናቸው)
- በበቆጂ ከሚገኙት ለተጠቃሚዎች ከተሰጡ ቤቶች 4ቱ (2 ባለ ሁለት መኝታና 2 ደግሞ ባለአንድ መኝታ ቤቶች) አስቀድሞ ዩኒቨርስቲው ከመቋቋሙ በፊት የተሰጣቸው የሶሻል

ሳይንስና የሂዩማኒቲ ኮሌጁ መምህራን በዩኒቨርስቲው ሥር ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ከ2 ዓመት በላይ በየወሩ የሚከፈላቸው የቤት አበል መቋረጥ ሲገባው አላግባብ በድጋሚ ለ4ቱም መምህራን በበጀት ዓመቱ ከህምሌ 1/08 - መጋቢት 30/09 (ለ9 ወራት) ብር 30,600.00 (800*9*3 + 1000*9*1) ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

- 156 ለተጠቃሚዎች ከተላለፉ ቤቶች ውስጥ የተለያየ ደረጃ ያላቸው ብዛታቸው 11 የሚሆኑት በአሰተዳደር ዘርፍ ለሚገኙ ሠራተኞች በኪራይ የተሰጡ ከመሆኑም በተጨማሪ የኪራይ ውል የሌላቸው መሆኑ፤ (4 ዶርሞች በብር 35.00፤ 2 ስቱዲዮ በብር 50.00፤ 3 ባለ 1 መኝታዎች በተለያየ ዋጋ አንዱ በብር 50.00 እና 2ቱ እያንዳንዳቸው በብር 100.00፤ 1 ባለ 2 መኝታ ቤቶች በብር 200.00)
- 1 ባለ2 መኝታ፤ 4 ባለ 1መኝታ፤ 6 ዶርሞችና ስቱዲዩ ቤቶች መምህራኑ የማይፈልጉአቸው መሆኑን ሳይረጋገጥ በአስተዳደር ሥራ ላይ ለተመደቡት የተሰጡ መሆኑ፣
- በ23/10/09 በተደረገ የመስክ ኦዲት ቅኝት ወቅት በግብርና ሳይት የሚገኙት ቤቶች የአብዘኞቹ ወደ ግቢ ለመግባት በማያስችል መልኩ በሳርና አረም የተከበበ፤ በዲንሾ ሳይት ደግሞ በተለይ አንዱ ብሎክ (ከመግቢያ በር አጠገብ ያለው) በየበረንዳው የተቀመጡ አርጌ ዕቃዎች፤ በመወጣጫው ግራና ቀኝ የተለያየ ቆሻሻ ነዋሪ ያለበት በማይመስል መልኩ የጽዳት ጉድለት እንደሚታይባቸው ጉዳዩ ከሚመለከተው የሥራ ክፍል ኃላፊ ጋር በመሆን ያረጋገጥን መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ተረጋጧል፡፡

8.2.2 <u>ስጋት፣</u>

- በኪራይም ሆነ በነጻ የመኖሪያ ቤት ከተሰጣቸው ተጠቃሚዎች ጋር ውለታ አለመኖር በቤቶቹ አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ክትትል ለማድረግና እርምጃ ለመውሰድ አያስችል፡፡ በቤቶቹ አያያዝና አጠቃቀም ላይ አለመግባባት ቢከሰት ተጠቃሚዎቹን ተጠያቂ ለማድረግና መፍትሄ ለመስጠትም አያስችልም፡፡
- ከፍተኛው ሀብት ወጪ ሆኖ የተሰሩ መኖሪያ ቤቶች ለተጠቃሚዎች ሳይተላለፉ ማቆየት ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል ከመሆኑም በተጨማሪ ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ (ተጠቃሚው ማን እንደሆነ) በባለሙያ ተገቢው ጥናት ሳይደረግ ጥገና ማከናወን የመንግስት ውሱን በጀት ለብክነት ይዳርጋል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው ከበቆጂ ከተማ አስተዳደር የተረከባቸው የመኖሪያ ቤቶች የርክክብ ሰነድ ለኦዲቱ ሥራ አለመቅረቡ እና በግቢው ውስጥ ሌላ ተጠቃሚ (የመብራት ምሰሶ

የሚያመርት ማህበር መኖር) እንዲሁም ቤቶቹ በአብዛኛው አገልግሎት ላይ አለመዋል በባለቤትነት ጥያቄ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

- ለመምህራን የመኖሪያ ቤት የተፈቀደው በመማር ማስተማሩ ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር ታስቦ በመሆኑ ቅድሚያ ለመምህራኑ መስጠት ሲገባ በአስተዳደር ዘርፍ ለተመደቡ ሠራተኞች ቤት መስጠት ቤቱ ከታለመለት ዓላማ ውጪ እንዲውል የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በአስተዳደር ሠራተኞቹ በተያዙት ቤቶች ዓይነትና ብዛት ለመምህራኑ ቢተላለፍ መንግስት አላግባብ ለመምህራኑ በየወሩ ከሚከፍለው የቤት አበል ወጪ ማዳን ይቻል የነበር፡፡
- ቤት የተሰጣቸው ተጠቀሚዎች ያለዩኒቨርሲቲው እውቅና ቤቱን ለሌላ ሰው ሲያስተላልፉ ወዲያውኑ እርምጃ አለመውሰድ የመንግስት ቤት ከታለመለት ዓላማ ውጪ እንዲውል ያደርጋል፡፡

8.2.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

- በመኖሪያ ቤቶቹ ላይ ከሚታዩ ግድፈቶች አንጻር ዩኒቨርሲቲው በመንግስት ንብረት ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በቤቶቹ አያያዝና አጠባበቅ ላይ በሚታዩ በእያንዳንዱ ግድፈቶች ላይ የሥራ አመራሩ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በቤቶቹ አያያዝና አጠባበቅ ላይ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8.2.4 **<u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>**

የሥራ አመራሩ በግኝቱና በማሻሽያ ሀሳቡ ላይ ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን የሚመለከተው የሥራ ክፍል፣

- በበቆጂ ካምፓስ ያሉት ቤቶችን በተመለከተ፡-
  - ሊያኖረን ከሚችል ደረጃ (ስታንዳርድ) በታች ናቸው በማለት መምህራን ሊኖሩባቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን፣
  - በግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅም ከቤቶቹ መጥበብ (አንድ ክፍል ከመሆናቸው) የተነሳ መምህራን ሊኖሩባቸው አለመቻላቸውን፣በዲንሾ ኮንዶሚኒየም ከሚገኙት ቤቶች መካከል ደግሞ 6ቱ ቤቶች ለስፔሻሊስት ሐኪሞች ለመጠባበቂያ የተቀመጡ ናቸው፡፡ ሌሎቹ የቀሩት የተደላደሉ ሲሆኑ፣ለትምህርት ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ የሄዱት ቤተሰቦቻቸው እየኖሩባቸው ነው::

- ያለ ዩኒቨርሲቲው እውቅ የሚኖርበትን አሳልፎ ለሌላ ግለሰብ የሰጠ መምህር ላይ እርማጃ ለመውሰድ በመጣራት ሂደት ላይ መሆኑን፣
- በግብርና ሳይት አካባቢ ከሚገኙ ቤቶች
  - ➢ ዶርሞች ለተጠቃሚ ያልተላለፉ ፈላጊ ስለአልነበራቸው መሆኑን፣
  - ➢ ባለ 2 መኝታ ቪላ ቤቶች 13ቱ ቀደም ሲል በTVET ሥር በነበሩ ጊዜ ውስጣቸው ፈርሰው ወደ መማሪያ ክፍልነት ተለውጦ የነበሩ ሲሆን፣ ዩኒቨርሲቲው ተመሥርቶ ከተረከቡ በኂላ ወደ መኖሪያ ቤትነታቸው ለመመለስ መልሶ ግንባታ መካሄዱን እና የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቀነስ በመልሶ ግንባታ ሂደት ለሁለት በመክፈል እንዲመቻች መደረጉን፣
  - ➢ አንድ ባለ 2 መኝታ ቤት ለዩኒቨርሲቲው ከተሠጠው አዲስ የግንባታ ይዞታ ላይ እንደነበረ፣ የኦሮሚያ መንገዶች ጥገና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሚኖርበት ለዩኒቨርሲቲው ለቆ ለጊዜው በምትክ እንዲኖሩበት በተገባ ውል የተቀመጠላቸው ቤት መሆኑን፣
- በቆጂ ካምፓስ ውስጥ ካሉት
  - ➢ 5ቱ ለአስተዳደር ሠራተኞች በጊዜያዊነት እንዲኖሩበት የተፈቀደ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ውል እንዲፈርሙ መደረጉን፣
  - ➢ ግቢው የከተማ አስተዳደር ስለነበረ ቀደም ተብሎ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የኮንክሪት ፓል ያመርቱበት ስለነበረ ይኸው ተጠናቆ እስኪለቀቅ እየተጠበቀ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው የበጀት እጥረት ስለገጠመው አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች እና ቅድሚያ ለሚሠጣቸው ከተማሪ አገልገሎት ጋር ለሚገናኙ ጥገናዎች (ዶርም፣ መመገቢያ ቤት፣ መማሪያ ክፍል) በጀት ተጠቅመው ስለነበረ የመምህራን ቤቶችን በተሟላ መልኩ ለመጠገን አለመቻላቸውን፣
- ከዩኒቨርሲቲው መኖሪያ ቤቶች መካከል 11ዱ የአስተዳደር ሠራተኞች ተከራይተው እንዲኖሩበት የተደረገው ከቤቶች መጥበብ የተነሳ መምህራን ስለማይፈልጓቸው መሆኑን፣
- 1 ባለ 1 መኝታ ለበጀትና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በነፃ ተሠጠ የተባለው ዳይሬክተሩ አካዳሚክ ስታፍ ስለሆነ መሆኑን፣

- በበቆጂ ካምፓስ ቤት እያላቸው ቤት አባል ሲወሰዱ የነበሩ እንዲመልሱ እየተደረገ መሆኑን፣
- የመኖሪያ ቤት አካባቢ ለታየው የጽዳት ችግር የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን፣

በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ማስታወሻ በተሰጠ ምላሽ ገልጿል፡፡

9. <u>የክትትል ኦዲት (Follow-up Audit) ፣</u>

9. <u>እርምጃ ያልተወሰደበት የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

9.1 <u>ግኝት፣</u>

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 የመንግስት መ/ቤት ኃላፊ በውጭ ኦዲተሮች እንዲሁም በውስጥ ኦዲት አገልግሎት በሚቀርቡ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የአርሲ ዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፣

- ከጤና ሳይንስ ኮሌጅ መጻህፍት በትውስት ወስደው ለዓመታት ያልመለሱ መምህራንና ሠራተኞች መጽሃፍቱን እንዲመልሱ በላይብረሪ ዳይሬክቶሬቱ በኩል ተደጋጋሚ ጥረት ተደርጎ ንብረቱ የሚፈለግባቸው መምህራንና ሠራተኞች ሊመልሱ ባለመቻላቸው ጉዳዩን ለውስጥ ኦዲት በማሳወቅ የውስጥ ኦዲት ክፍሉም እርምጃ እንዲወሰድ ለዩኒቨርሲቲው ሪፖርት ቢያደርግም አመራሩ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

9.2 <u>ስጋት፣</u>

በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሃሳብ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ እርምጃ አለመውሰድ የመንግስት ንብረት ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዲውል መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊሚፈጥር እና መንግስትን ለሌላ ተጨማሪ ወጪ ሊጋብዝ የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ የወጣባቸው በመሆኑ በኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ የሥራ አመራሩ፣ የዩኒቨርስቲው ቦርድና የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

9.3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ በግኝቱ እና በማሻሸያ ሀሳቡ ላይ ምላሽ አልሰጠም፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!!

አባሪ ቁጥር 1 የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ የተፈፀመ ግዜያዊ ቅጥር

ተ.ቁ	ስም	የስራ ሃላፊነት	የገንዘብ መጠን
1	Shelema Habtamu	የነፃ ህግ አገልግሎት ሰራተኛ	7,000.00
2	Baysa Seboka	>>	7,000.00
3	Sisay Negess	>>	7,000.00
6.4	Fenose Teshene	>>	7,000.00
5	Melik Beshir	>>	5,600.00
6	Yoobsan Abera	>>	4,666.67
7	Wኦሮku Dadi	>>	4,666.67
8	Chala Bidira	>>	4,666.67
9	Sultan Bekera	>>	4,666.67
10	Abebe Hailu	>>	4,666.67
11	Boja Tesfaye	>>	3,500.00
12	Belay Feleke	>>	2,333.33
13	Deme Tades	>>	3,500.00
14	Zelalem Tesfay	>>	3,500.00
		ድምር	**69,766.68**

አባሪ ቁጥር 2 - ያላግባብ የተፈፀመ የፕሮፌሽናል ክፍያ

I/no	Name	Academic rank	thesis advisኦሮ	internal examiner	External examiner	Chairpers on /proposal review/	Total Amount
1	Mesay mulugኢትa	አሰs/prof	21,600.00	6,000.00	-		27,600.00
2	Hurgesa Hundera	Lec		7,500.00			7,500.00
3	Tefaye Genemo	Lec	17,280.00	7,500.00			24,780.00
4	Cherinኢት Abebe	Lec				4,500.00	4,500.00
5	Gezmu Hundu	Lec	21,600.00	7,500.00			29,100.00
6	Tsኢትadrgachew legese	Lec	12,960.00	7,500.00			20,460.00
7	Negአሰho Bedአሰa	Lec				4,500.00	4,500.00
8	Teshome Beyene	Lec				4,500.00	4,500.00
9	Ayalew bekele	Lec				4,500.00	4,500.00
11	Abdi yuya	Lec				4,500.00	

				7,500.00			12,000.00
12	Hailu Abera	Lec				6,750.00	6,750.00
16	Daniel G/Tsadik	አሰs/prof			6,000.00		6,000.00
17	D/r Kenate Wአሮku	አሰs/prof			6,000.00		6,000.00
18	D/r Desalegn Yaheh	አሰs/prof			6,000.00		6,000.00
19	D/r Abiot Legese	አሰs/prof			6,000.00		6,000.00
20	D/r Abayneh Ayele	አሰs/prof			6,000.00		6,000.00
21	D/r Tesfaye Muye	አሰs/prof			6,000.00		6,000.00
22	D/r Bogale Teferi	አሰs/prof	4,320.00				4,320.00
23	D/r Teferi Mekonnen	አሰs/prof	21,600.00				21,600.00
24	D/r Dugአሰsa Mulugኢ.ትa	አሰs/prof			6,000.00		6,000.00
25	D/r Solomon Alemu	አሰs/prof		6,000.00			6,000.00
26	D/r Tolessa Alemu	አሰs/prof			7,500.00		7,500.00
27	D/r Gኢ.ትu Tአሰso	አሰs/prof	8,640.00				8,640.00
28	Kአሰsahun Dubale					4,500.00	4,500.00
						Total	**240,750.00**

<u>አባሪ ቁጥር -3 በዕቃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ያልተረጋገጠ እና የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የቀረበለት መድሃኒት ግዥ</u>

ተ/ቁ	የዕቃው ዓይነት	የቫውቸር ቁጥር	በዕቃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ያልታየ	የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የቀረበለት
1	መድሃኒት	954824	2,150,090.00	1,367,772.14
2	››	958679	1,492,957.51	1,106,945.05
3	››	954715	398,412.32	398,412.32
		ድምር	**4,041,459.83**	**2,873,129.51**

አባሪ ቁጥር-
4 የበጀት ንፅፅር

ተ/ቁ	የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ስራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት	ከበጀት በላይ የወጣ	ያልተሠራበት በጀት (በ%)
1	6114 - Wages to Cአሱual Staff	3,014,745.70	3,075,907.40	-	61,161.70	
2	6116 - Miscellaneous Payments to Staff	35,084,922.99	35,196,545.69	-	111,622.70	
3	6121 - Allowance to Permanent Staff	8,453,815.88	8,777,008.66	-	323,192.78	
4	6131 - Government Contribution to Permanent Staff Pension	16,032,656.79	16,170,124.37	-	137,467.58	
5	6211 - Unifኦርms, Clothing, Bedding	12,450,613.60	12,921,591.76	-	470,978.16	
6	6212 - Office Supplies	4,419,499.00	3,779,691.07	639,807.93		14.48
7	6216 - Food	20,457,900.00	22,442,017.74	-	1,984,117.74	
8	6217 - Fuel and Lubricants	5,940,000.00	5,945,031.97	-	5,031.97	
9	6219 - Miscellaneous Equipment	1,358,900.00	944,425.67	414,474.33	-	30.50
10	6221 - Agriculture, Fኦርestry and Marine Inputs	327,568.00	184,570.98	142,997.02	-	43.65
11	6222 - Vኢትerinary Supplies and Drugs	360,000.00	312,343.83	47,656.17	-	13.24
12	6223 - Research and Development Supplies	2,324,384.00	5,009,197.93	-	2,684,813.93	
13	6231 - Per Diem	17,462,554.00	19,120,902.27	-	1,658,348.27	
14	6233 - Official Entertainment	4,794,340.00	5,100,038.41	-	305,698.41	
15	6241 - Maintenance and Repair of Vehicles and Other Transpኦርt	8,048,171.07	8,059,113.16	-	10,942.09	

16	6244 - Maintenance and Repair of Buildings, Furnishings and Fixtures	7,790,396.00	6,892,430.78	897,965.22	-	11.53
17	6251 - Contracted Professional Services	4,918,980.00	5,216,335.23	-	297,355.23	
18	6252 - Rent	8,187,661.50	8,395,379.46	-	207,717.96	
19	6253 - Advertising	673,696.00	537,139.85	136,556.15	-	20.27
20	6254 - Insurance	1,016,530.00	822,957.98	193,572.02	-	19.04
21	6255 - Freight	508,996.00	581,160.19	-	72,164.19	
22	6256 - Fees and Charges	979,505.00	727,458.04	252,046.96	-	25.73
23	6257 - Electricity Charges	3,660,000.00	3,246,072.78	413,927.22	-	11.31
24	6259 - Water and Other Utilities	1,796,087.60	2,031,127.51	-	235,039.91	
25	6271 - Local Training	4,159,149.00	4,311,686.59	-	152,537.59	
26	6314 - Purchአሰe of Buildings, Furnishings and Fixtures	84,295.00	15,670.21	68,624.79	-	81.41
27	6412 - Grants, Contributions and Subsidies to Institutions and Enterprises	3,147,476.00	3,276,500.33	-	129,024.33	
28	6417 - Grants and Gratuities to Individuals	3,900,231.99	3,945,535.85	-	45,303.86	
	Total	181,353,075.12	187,037,965.71	3,207,627.81	8,892,518.40	

አባሪ ቁጥር 7 - ተሽከርካሪ መኪዎች			
ተ.ቁ	የተሽከርካሪው ዓይነት	የሰሌዳቁጥር	መግለጫ
1	ሎንግ ቤዝ	4-05429 ኢት	ሊብሬ የሌለው
2	Motኦሮcycle	4-0312 ኢት	ሊብሬ የሌለው
3	Motኦሮcycle	4-0779	ሊብሬ የሌለው
4	Motኦሮcycle	4-1135	ሊብሬ የሌለው
5	Tractኦሮ	1034	ሊብሬ የሌለው
6	Tractኦሮ	50	ሊብሬ የሌለው
7	Tractኦሮ	53	ሊብሬ የሌለው
8	Tractኦሮ	27	ሊብሬ የሌለው
9	Tata መለስተኛ አውቶቡስ	4-17372 ኢት	ሊብሬ የሌለው
10	Sun long s/Bus	4-17607 ኢት	ሊብሬ የሌለው
11	Sun long	4-16597 ኢት	ሊብሬ የሌለው
12	Scania	4-000366	ሊብሬ የሌለው
13	Scania	4-00354 አሰ	ሊብሬ የሌለው
14	Toyota	4-02246 ኦሮ	ሊብሬ የሌለው
15	Minibus	4-23710	ሊብሬ የሌለው
16	Toyota St/w	4-23355	ሊብሬ የሌለው
17	d/pikup	4-23554	ሊብሬ የሌለው
18	ሎንግ ቤዝ	4-03720	ሊብሬ የሌለው
1	Iveco Mini bus	4-07077 ኢት	ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት/ኖርማላይዜሽን/ የሌለው
2	Isuzu የጭነት መኪና	4-01125	>> >>
3	Fኦሮd pickup	4-018854	>> >>
4	Fኦሮd	4-02722 ኦሮ	>> >>
5	ሎንግ ቤዝ	4-00234	>> >>
6	ሎንግ ቤዝ	4-05429	>> >>
7	አውቶቡስ	4-08508	>> >>
8	Motኦሮcycle	4-0780	>> >>
9	Motኦሮcycle	4-0799	>> >>
10	Motኦሮcycle	4-0312 ኢት	>> >>
11	Motኦሮcycle	4-0779	>> >>
12	Motኦሮcycle	4-0784	>> >>
13	Motኦሮcycle	4-1135	>> >>
14	Tractኦሮ	1034	>> >>
15	Tractኦሮ	50	>> >>
16	Tractኦሮ	53	>> >>
17	Tractኦሮ	27	ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት /ኖርማላይዜሽን/ የሌለው
18	Mercedes bus	4-08552 ኢት	ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት /ኖርማላይዜሽን/ የሌለው
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት